# አምባአራዶም

አምባራዶም ላይ የራስ ሙሉጌታ ጦር ሠፍሯል ። ኢጣሊያኖቹ እንደገመቱትና እንደጻፉት አምባራዶም ያለው የራስ ሙሉጌታ ጦር 80.000 ወታደር ፣ 400 መትረየስ ፣ አስር መድፍና የአይሮፕላን መቃወሚያ አርሊኮን አላቸው ይላሉ ። ተምቤን አውራጃ ውስጥ ከተደረጉት ጦርነቶች በፊት ባዶሊዮ የራስ ሙሉጌታን ሠራዊት ለመምታት አስቦ ነበር ።ምክንያቱም የራስ ሙሉጌታ ጦር አስፈርቶት ነበርና ነው ።

ባዶሊዮ ለሙሶሊኒ ባስተላለፈው ቴሌግራም «.....ካሉት የጦር አዛዦች አስ ፈሪው ሙሉጌታ በመሆኑ የሱ ኃይል ከባድ ነው ። ሰውየው ቀላል አይደለምና ምንም ይሁን ምን ሳይፈራ ይዋጋናል ።...ከሱ ጋር የምናደርገው ውጊያ ቀላል ያለ መሆኑንና እጅግ በጣም ጠቃሚ መሆኑንም እንዲያውቁት ።...» ሲል ገለፀ ። የኢ ጣሊያ አየር ኃይል አምባራዶምንና አካባቢውን ፎቶግራፍ አንስቶ ስለመጣ የጦሩ ፕላን በዝርዝር ተዘጋጅቷል ። ሌላው ቀርቶ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከቦምብ ለመጠ ለያ የቆፈረው ዋሻና የራስ ሙሉጌታ ዋሻ በፎቶግራፍ ቁልጭ ብሎ ተነስቷል ።

ጠቅላይ ሠፈሩን እንዳየሱስ ላይ ያደረገው ባዶሊዮ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሲሰጥ «....ወደ አዲስ አበባ የሚያስኬደን መንገድ እየተዘጋ አስቸግሮናል ። በተለይ ለአዲስ አበባ ጉዞአችን መሰናከል የሆነው የአምባራዶም ምሽግ ነው ። ...በዚያ ያለውን የሙሉጌታን ጦር ለመምታት ወስኛለሁ ።... » ብሎ ተናገረ ። ከዚህ መግለጫ በኋላ የጦር መኰንኖቹን ሰብስቦ «...የራስ ሙሉጌታን ጦር ለመምታት ወስኛ ለሁ » ብሎ ያንኑ ቃል ደግሞ ከተናገረ በኋላ «... ነገ ፌብሩዋሪ 10 (በኛ የካ ቲት 3) ለዋ 1ኛው ክፍለ ጦር አሁን ካለበት ተንቀሳቅሶ የቻለውን ያህል ወደፊት እንዲገፋ ፣ በማግሥቱ ፌብሩዋሪ 11 ቀን 1ኛውና 3ኛው ክፍለ ጦሮች በሁለት አቅጣጫ ወደ እንጣሎ እንዲጓዙና ከአምባራዶም በስተደቡብ እንዲሠፍሩ ።.... ጠቅላላ 70.000 ወታደር ያለበትንም የጦር እንቅስቃሴ እኔ እመራለሁ ።....ወዳጆቼ ሆይ ፣ ችግር ያጋጥማችኋል ። የሆነው ቢሆን ይህን ጦርነት ማሸነፍ አለብን ። ወዳ ጆቼ ፣ ይህ ዘመቻ ከናፖሊዮን ጦርነት ወዲህ ያልታየ ነው ። ሁለት ወር በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደትቢያ ሲበን ታዩታላችሁ ። ...አላቸው ...» ሲል ቶማሴሊ ጽፏል ።

የካቲት 3 ቀን 1ኛውና 3ኛው ክፍለ ጦር ቀለሚኖ እና ገባ የተባሉትን ወን ዞች ተሻገረ ። በነጋታውም ጉዞውን ቀጥሎ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሠፈር ሲታየው ጉዞውን አቆመ ። በዚህ የወታደሩ ጉዞ የተደሰተው ባዶሊዮ አምባ ገዳም ላይ ሆኖ የጦር መኰንኖቹን ሰብስቦ «...ታድያስ መኳንንቶች ? አሁን ደስ አላችሁ ?ስለሚካ ሄደው ትርኢት ጥሩ ጥሩውን ታዩ ጀመር ። አዎን ድራማው በብዙ ክፍሎች የተ ከፋፈለ ነው ። ያሁኑ የድራማው መነሻ ነው ። ወታደሮቻችን አስደናቂ ጉዞ ተጉ ዘዋል ። ዛሬ ጧት በ0900 ሰዓት ግንባር ቀዳሚው ጦራችን አስፈላጊዎቹን ቦታ ዎች ሁሉ ይዘዋል ...ብሎ ነገራቸው...»ሲል ቶማሴሊ ጽፏል።

የወታደሮቹ መግፋት ባዶሊዮን ቢያስደስተውም የኢጣሊያን ጦር መጠጋት ያየው የኢትዮጵያ ሠራዊት የካቲት 5 ቀን ጦርነቱን አንስቶ ከባድ ውጊያ ጀመረ። ስለዚያ እለቱ ውጊያ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ታሪክ የሚሆነው ባዶሊዮ በመጽሐፉ የገለፀው ነው ። እንዲህ ይላል ።«....ፌብሩዋሪ 12 ቀን የኛን ጦር ገፍቶ መስ...

ኢትዮጵያውያን ባዩ ጊዜ እንዲጋብር በሠፈረው 3ኛ ጃንወሪ (በሚባለው) ዲቪዚ የናችን ላይ ተኩስ ከፈቱበት ። ባለጥቁር ሸሚዞችንም ወደፊት እንዳይገፉ ገትረው ያዙዋቸው ።...የጦር አዛዦቻችን በጦር ፕላን ለማዘዝ እስቲቸገሩ ድረስ ኢትዮጵ ያውያን ግራ አጋቡዋቸው ።...»

በቀጠሉት ቀናትም ማለት የካቲት 5 እና 6 ቀን ኢትዮጵያውያኖች ገትረው ያዙ ። ቶማሲሊ በመጽሐፉ«....ያስቸገሩት ፈረሰኞቹ ኢትዮጵያውያን ተዋጊዎች ነበሩ ። በእነዚያ ሁለት ቀናትም እነኚያን ፈረሰኞች ጋብ ሊያደርጋቸው የቻለው እንዶዝናብ የወረደባቸው የመድፍ ጥይት ነው ።...አበሾቹ ፣ ኢጣሊያኖቹን የሚዋጉት በጠራ ዘመናዊ መሣሪያ አይደለም ። በባለ ጥቁር ባሩድ ጥይትና ባሮጌ ጠመንጃ ነው ። እልፎ እልፎ ብቻ አንዳንዱ የመትረየስ ድምፅ ይሰማል ። እንዲህ ዓይነቱን አሮጌ መሣሪያ ይዞ ዘመናዊ መሣሪያ ያለውን ዘመናዊ ወታደር መግጠም ምን ተስፋ አለው? የሚገርመው ነገር ፣ አበሾቹ ጕራዴያቸውን መዝዘው ይይዙና በብዛት ሆነው እየተሯሯጡ ከኛ ጦር ውስጥ ይገባሉ ። ከዚያም የኛን ወታደር ከፋፍለው ባያለበት ያሽብሩታል ። በጠመንጃ ከሚታኰሱት ይልቅ እንደ አገራቸው ልምድ በሚዋጉት በእንዲህ ዓይነቱ ውጊያ እጅግ በጣም አደገኞች ናቸው ።...» በማለት የጊዜውን ውጊያ ያብራራል ።

ጠቅላይ ሠፈራቸውን አምባራዶም ላይ ያደረጉት ራስ ሙሉጌታ የኢጣሊያን የጦር ወታደር ብቻ ሣይሆን የጦር አዛዦን ባዶሊዮንም ጭምር ግራ አጋቡት ። ባዶሊዮ ፕላን አውጥቶ ጦሩን በፕላኑ መሠረት እንዲዋጋ ሲያዝ ፣ ሙሉጌታ ሌላ እቅጣጫ ፈጥረው ባዶሊዮ በፕላን የያዘው ቦታ ባዶ ይሆናል ። በዚህ ዓይነት ዘዴ ራስ ሙሉጌታ ስላስቸገሩ ባዶሊዮ ፕላን የሌለው ጦርነት ለማድረግ ወሰነ ።

የካቲት 7 ቀን 1928 ዓም ከጧቱ በአንድ ሰዓት የኢጣሊያ ጦር በሙሉ ወደ ፊት ገፍቶ አምባራዶምን እንዲከብና በሰማይ ድጋፍ ሰጭ አይሮፕላኖችም የራስ ሙሉጌታን ሠራዊት ንቅናቄ እንዲደበድቡ አዘዘ ። በትእዛዙ መሠረት የካቲት 7 ቀን ጦርነቱ ሲካሄድ የኢጣሊያ ጦር ቢያይልም በራስ ሙሉጌታ ውስጥ የነበሩት በደጃዝማች ገብረ ሚካኤል ፣ በፊታውራሪ አውራሪስ ፣ በፊታውራሪ ወልደማርያምና በፊታውራሪ ኪዳኔ የሚመራው ጦር ቀኑን ሙሉ በሩን ዘግቶ ኢጣሊያኖች ራሳቸው እስቲደነቁ ድረስ አልበገር ብሎ ዋለ ። በመጨረሻም ባዶሊዮ ምርጥ የአይሮፕላን መትረየስ ተኳሾችንና በምብ ጣዮችን አስነስቶ የኢትዮጵያን ጦር በሰማይም በመሬትም በመትረየስና በቦምብ ያስደበድብ ጀመረ ። በዚህም ከባድ ጦርነት የኢጣሊያ ጦር መንገድ እያስለቀቀ አምባራዶም ግርጌ መድረስ ቻለ ። ከዚህ በኋላ አምባራዶም ተራራ በቦምብ እየተደበደበ በሙሉ ተቃጠለ ። ከኢትዮጵያ ሠራዊትም ያለቀው አልቆ የተረፈው ሸሸ ።

«....አምባራዶም ተራራን ፀሐይዋ ሳትጠልቅ ያዝነው ። የአምባራዶም በር በመከፈቱ በጣም ደስ ቢለኝም የኢትዮጵያ ወታደር ከተራራው በማምለጡ ግን ከፋኝ። ከሌላ ዘንድ ተሰልፈው እንደሚቆዩም ታወቀኝ ።...» በማለት የጻፈው ባዶሊዮ ከተራራው አምልጠው በወረዱ አንድ ሺ የማይሞሉትን ሰዎች አየር ኃይሉ እየተከታተለና እየፈለገ እንዲደበድብ ታዘዘ ። የኢጣሊያ አየር ኃይልም አራት ቀን ሙሉ በሰሜን እየተዘዋወረ በኮረብታዎች፣ በተራራዎች፣ በሸለቆዎችና የእግር መንገዶች በታዩበት ሁሉ ቦምብ በመጣል ደበደበ ። በሹም ሽሩ የከፋቸው ራስ ሙሉጌታና ሠራዊታቸው ግን አልተገኘም ። ሳመለጠው የራስ ሙሉጌታ ሠራዊት ...ጣለው ቦምብ «...40 ቶን የሚመዝን ነው ...» ሲል ፓውል ጀንቲዚዮን ይገልፃል ። ...«...አበሾቹ የት እንደገቡ ጠፉ ። አይሮፕላኖቻችን ከጧት እስከ ማታ ሲፈልጓቸው ...። ግን ምልክታቸው እንኳ አይገኝም ። ... » ሲል መስክሯል ።

የራስ ሙሉጌታ ጦር የተጓዘው ወደ አዘቦ ነበር ። የራስ ሙሉጌታ ሠራዊትም እየተከላከለ ሲጓዝ ራስ ሙሉጌታ ልጃቸውን ከጦሩ መሀል አጡት ። ሲያውም ልጄን ጥዬ አልሄድም ብለው ልጃቸውን የሚፈልግ መላክተኛ ወደኋላ መልሰው ላኩ ። የተላኩትም መልእክተኞች ሲመለሱ የልጃቸውን መሞት ነገሯቸው ። ራስ ሙሉጌታም የልጃቸውን መሞት እንደሰሙ የልጄን ደም እበቀለሁ ብለው ወደኋላ ተመለሱ ። በዚህ ጊዜ የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ደርሰው በኋላ ልብሳቸው ለይተው አውቀዋቸው በመትረየስ በአሩምታ ተኩስ መቱዋቸው ። ሙሉጌታም ቆስለው ወድቀው በኋላ ሞቱ ።

የአምባራዶም ጦርነት ለመጨረሻ ጊዜ የካቲት 12 ቀን 1928 ዓ.ም ተፈፀመ ። በዚህ ጦርነት ጠቅላይ የጦር አዝማቹ ባዶሊዮ እንደሚገልፀው "...36 ነጭ መኰንኖች ፣ 621 ነጭ ወታደሮች ፣ 145 ጥቁር ወታደሮች ሞተዋል..." ይልና የኢትዮጵያውያኑን ሟቾች ቁጥር 6.000 ያደርሰዋል ። በዚህ ውጊያ ከኢጣሊያ በኩል 23.000 የመድፍ ጥይት ተተኩሷል ። 170 አይሮፕላኖች እየተመላለሱ 396 ቶን የሚመዝን ከባድ ፈንጂ ጥለዋል ። ስለ አየር ኃይሉ ተግባር ፓውል ጄንቲዚዮን ሲጽፍ "…. የአየር ኃይሉ ጀግንነቱን እንደገና አስመሰከረ ።... ለአየር ኃይሉ የጠቀመው ሠፈሩ ወይም መነሻውና መመለሻው መቀሌ ላይ መሆኑ ነው ። ከመቀሌ እምባው ድረስም ርቀቱ 15 ማይል ያህል ነው ። ቦምብ ሲጥል የሄደው ጥሎ ከመመለሱ በፊት የሚነሣው አይሮፕላን ይነሳል ።…." ብሏል ።

ጄኔራል ባስቲኮም በመጽሐፋቸው "…. የኢጣሊያ አየር ኃይል እንቅስቃሴ ባየ ቁጥር ቦምብ ይጥል ስለነበር እልፍ እልፍ የወገኑ" ጦር ይደበድብ ነበር ።... በ28ኛው የሕክምና ቡድን ሰፈር ላይ አንዲት የኢጣሊ' አይሮፕላን አምስት ቦምብ ጣለች ። በሕክምናው ቡድን ሠፈር በሕይወት የተረፈ አንድም ፍጡር አልተገኘም ። አንድ መቶ ሰዎች ያህል ተገደሉ ።……." ብለው ፃፈዋል ። በመጽሐፋቸው ሌላ ገጽ ላይ ደግሞ "…….በዚያ በአምባራዶሙ ውጊያ ዮቂት አበሾችን ማርከን ነበር ። አንድ የኢጣሊያ መኰንን አንዱን የአበሻ ምርኮኛ ሊመረምር ኢጣሊያት ትዕግሥቱ አለቀ ። ኢትዮጵያዊው ምርኮኛ ሶስት ቦታ ላይ ቆስሏል ። መኰንኑም ያን ምርኮኛ ለማስፈራራት እየጮኸበት በአስተርጓሚ ይጠይቀዋል ። ኢትዮጵያዊው ምርኮኛ ግን በአስተርጓሚው አማካኝነት አላውቅም ከማለት ሌላ መልስ አይሰጥም ። ከሶስት ቦታ በቆሰለው ቁስሉ ላይ መድኃኒት አልተደረገለትም ። የቁስሉንም ፣ የመኰንኑንም ጩኸትና መከራ ችሎ ፀጥ ብሏል ። መርማሪው መኰንንም የሚያደርገውን ቢያጣ 'እነኚህ የአበሻ ወታደሮች ለጌቶቻቸው እንደ ውሻ ታማኝ ናቸው' ብሎ በማድነቅ ተወው ። ..." ሲሉ ጽፈዋል ።

—O—



እግረኛው ወደአምባራዶም ሲጓዝ ።




28 ኦቶብሬ ብርጌድ አምባራዶም ላይ ሲዋጋ ።



በአምባራዶም የኢጣሊያ ምሽግ ።



በአምባራዶም ካሚቹ ኔሪ ወታደሮች ።




በአምባራዶም የኢጣሊያ መድፈኞች መድፍ ሲቀኩሱ ።




ከባዙቃ ተኳሾች አንዱ ።



ለጦር እቅድ በኢጣሊያ አይሮፕላን ፎቶግራፍ የተነሳው የአምባላጌ ተራራ ።




እምባላጌ ዙሪያውን በአይሮፕላን ቦምብ ተደበደበ ።




የአምባላጌው መትረየስ ተኳሽ ።



፩ኛው ባታሊዮን የባላገሩን ቤት እያቃጠለ ሲገባ ።



የ28 ኦቶብሬ ባታሊዮን ጦር ሠፈር



ራስ ሙሉጌታ

# ሽ ሬ

በሽሬ በኩል እንዲዘምቱ የታዘዙት የጐጃም ገዥ የነበሩት ራስ እምሩ ነበሩ ። የደይሊ ቴሌግራፍ ጋዜጠኛ ራስ እምሩን ስለ ዘመቻው ሁኔታ ጠይቋቸው ነበር ። "....ወደ ሽሬ እንድዘምት ንጉሡ አዘዙኝ ። በክተት አዋጅ ከግዛት አውራጃዬ 25.000 ሰዎች ተሰበሰቡ ። ደጃች አያሌው ብሩ ከበጌምድር ከአስር ሺህ ያልበለጡ ሰዎች ሰበሰቡ። ከዚህ በተረፈ ባንዳንድ አለቆች አምስት ሺ ያህል ሰዎች ተሰበሰ ቡና በጠቅላላው አርባ ሺ ያህል ሰዎች ያዝኩ ። ዋና የጦር ሠፈራችንን ደብረ ማር ቆስ ላይ አድርገን ተዘጋጀን ። በታህሣስ ወር መጀመሪያ ላይ ጉዞ ጀምረን ዳባት ስንደርስ አይሮፕላን መጣብንና ለሚጥለው ቦምብ ኢላማ ሆንለት ። እንዲህ ዓይነቱ ዘመቻ የመጀመሪያ ጊዜያችን ስለነበረ ወዲያው ብትንትናችን ወጣ ።

"...ደጃዝማች ገሠሠም ፊቱን አዙሮ ወደ ጐጃም በሽሽት ሲመለስ አየሁት ። እሱ ብቻ አይደለም የሸሸው ። አብረውት የነበሩት የጦር አዝማቾች በሙሉ ሲሸሹ ከአጠገቤ ከአስር ሺህ ሰዎች ጋር የተገኘው ደጃዝማች አያሌው ብሩ ብቻ ነው ። እንደምንም ብለን ተከዜ ወንዝ ስንደርስ ወታደሮቼን ባስቆጥራቸው የተረፈኝ ወታ ደር ከጐጃም ስነሳ ከነበረኝ ግማሹ ብቻ ነው ።..." በማለት ልዑል ራስ እምሩ የተናገሩትን ዴይሊ ቴሌግራፍ ጋዜጣ አውጥቶታል ።

የራስ እምሩ ጦር ተከዜን ተሻግሮ ማይ ጥምቀትና አዲ አጨብ ላይ መሸገ። ባንዱ ቦታ አንድ ሺህ ፣ በሌላው ቦታ ሁለት ሺህ ሰዎች ከመሸጉ በኋላ ሌላው ሠራ ዊት ወደ እንዳባጉና ተጉዞ የኢጣሊያ ወታደር ሊያልፍ የሚችልበትን መንገድ ይዞ ሙሸገ። የእንዳባጉና በር መያዙ በኢጣሊያኖች ዘንድ እንደተሰማ በሜጀር ክሪኒቲ የሚመራው ጦር በሩን እንዲያስለቅቅ ታዘዘ ።

ሜጀር ክሪኔቲ በዘጠኝ ታንኮች የተጠናከረ ጦሩን ልኮ ታህሳስ 6 ቀን 1928 ዓ.ም. ፀሐይዋ ስትግል ጦርነቱ ተጀመረ ። ኢትዮጵያውያኖቹም የኢጣሊያን ጦር ዙሪያውን ከበው ፈጁት ። የተላኩትንም ዘጠኝ ታንኮች በጣጥሰው ጣሉዋቸው ። ይህን ያየው ሜጀር ክሪኔቲ እግረኛው ጦር ተደባልቆ በጩበጣ እንዲዋጋ አዘዘ ። ከዚህ በኋላ የደምቢጉና መሬት በሬሣ ተሞላ ። ኢጣሊያኖቹ እንደገለጡት በዚያች ቦታ ዘጠኝ ሙኰንኖች ፣ 22 ኢጣሊያዊ ወታደሮችና 370 ጥቁር ወታደሮች ከኢ ጣሊያ ወገን ተገደሉ ። ከኢትዮጵያውያኖችም አምስት መቶ ሰዎች ሞቱ ።

ስለዚያ ቀኑ ጦርነት ራስ እምሩ ሲናገሩ "....ትልቅ ጦርነት ነበር ። እኛም ካለን ብዙ ጠመንጃ ሌላ አምሳ መትረየሶች ይዘን ነበር ። በዚህም ጠላትን አባረርነው ።..." ሲሉ ፣ ባዶሊዮ ደግሞ "....ባናጋንነውም በጦር አዛዦቻችን ስህተት ጠላት ድል ሊያ ደርገን ችሏል ።...." ብሏል ።

በደምቢጉና ውጊያ የተደናገጠው ባዶሊዮ ሁለት ክፍለ ጦር ወደ ቦታው ተልኮ የራስ እምሩን ሠራዊት እንቅስቃሴ እንዲያቆም አዘዘ ። ይህም የታዘዘው አጠናካሪ ጦር ከደረሰ በኋላ ታህሣስ 13 ቀንና ታህሳስ 16 ቀን አፍጋጋ እና ፀለሌ በተባ ሉት ቦታዎች ላይ ከባድ ውጊያ ተደረገ ። አሁንም ኢትዮጵያውያኖቹ ድል አደረጉ ። በዚህ በኢትዮጵያውያኖቹ ድል ማድረግ የተበሳጩት ሙሶሊኒ "... ባዶሊዮ የማ ይረባ ሰው ስለሆነ ሊያዋርደን ነውና በሱ ቦታ ጀኔራል ግራዚያኒ ተተክቶ ጠቅላይ አዛዥ ይባል ።..." ብለው የጦር ሚኒስትራቸውን አዘዙ ። በዚህ ሹም ሽር የባዶ

ሊዮን መበሳጨት የሰማው የጦር ሚኒስትሩ በምክርም በክርክርም ዱቼ ሙሶሊኒን አግባብተው ባዶሊዮ ጠቅላይ አዛዥነቱን ይዞ እንዲቆይ አደረገ ።

ስለ ታህሣስ 13 ቀኑና ስለቀጠለው ውጊያ ራስ እምሩ ለአንጂሎ ዴል ቦካ ሲያጫውቱት "....አሳዛኝ ትርኢት ነበር ። እኔ ራሴ ለጥቂት ነው ከሞት ያመለጥኩት ። ታህሣስ 13 ቀን ጧት ብዙ የጠላት አይሮፕላኖች ሲመጡብን አየን ። እንደ ደረሱም ቦምብ ይጥሉብን ጀመር ። ቦምቡ የተለየ ነው ። ሠራዊቱ ሁሉ ይወድቃል ። ወደ ወንዝ በመሮጥ ውሃ በእፍኙ እየዘገነ የተቃጠለ ከንፈሩን ያርሳል ። በዚያው በወንዙ ዳርም እየተፈነገለ ይወድቃል ። ለጥቂት ሰዓታት በስቃይ ይቆዩና ይሞታሉ። ካለቁትም ሰዎች መሀል ጦረኞች ሳይሆኑ በአካባቢው የሚኖሩና ከብቶቻቸውን ውሃ ለማጠጣት የመጡት ሁሉ ናቸው ። የጦር አለቆቹ ተሰብስበው ምን እናድርግ ? ብለው ጠየቁኝ ። የምመልስላቸው ነገር ቸገረኝ ። ከሚያቃጥልና ከሚገድል ዝናብ ጋር ሰው እንዴት ጦርነት መግጠም ይችላል ?...." ብለውታል ።

የኢትዮጵያውያኖች የነበረው ድል በመርዝ ጋዝ ምክንያት የኢትዮጵያ ሠራዊት ተበታተነ ። ቢሆንም የጦር ሰፈሩ ወደ ማይላህላ ተዛውሮ ከሞት የተረፈው ሠራዊት እንዲሰበሰብና እንዲከት ሆነ ። በአይሮፕላኑ ቦምብና በመርዙ ጋዝ ተደናግጦ የተበታተነው የኢትዮጵያ ሠራዊት መሰንበቻውን ሲሰባሰብ ከረመ ። ከጦሩ ቦታ ያልነበረና ለውጊያው ያልደረሰው ሠራዊት ሁሉ ሲሰበሰብ ቆየ ። ራስ እምሩም ጦራቸው እስቲጠናከር በደፈጣ ቆዩ ።

ራስ እምሩ የራስ ካሣን ድል ሆኖ ከጦር ግንባር መመለስ እንደሰሙ ማይላህላ ላይ የጦር አዛዦቻቸውን ሰብስበው ተማከሩ ። በስብሰባውም ስማማ ፥ አዲ ሃይማናልና ሰለክላካ የመሸገው ጦር እንዳለ ሆኖ ለሚቀድመው ጦር ደጀን እንዲሆን ፥ ጓዝና ሃያ ሺህ ጦር ደግሞ ተከዜ ላይ እንዲቆይ ተወሰነ ።

በኢጣሊያም በኩል በጀኔራል ማራቬኛ የሚመራው 2ኛው ክፍለ ጦርና በጀኔራል ሳቢኒ የሚመራው 4ኛው ክፍለ ጦር የራስ እምሩን ሠራዊት እንዲዋጋ ታዘዘ ። በእነዚህ ሁለት ክፍለ ጦሮች ውስጥም 47.000 ወታደሮች አሉበት። የነዚህም ወታደሮች ብዛት ከራስ እምሩ ወታደር በመሣሪያ ብቻ ሳይሆን በብዛትም ይበልጣል ። ለእነኚህ ሁለት ክፍለ ጦሮችም ደጀን እንዲሆን በጀኔራል ፊዴንዚዮ ዳል ኦራ የሚመራው ክፍለ ጦር ተመደበ ።

የኢጣሊያን ጦር ዝርዝሩን ብንመለከት በ1ኛው ክፍለ ጦር ውስጥ ብቻ 2.500 መኰንኖች ፥ 50.000 ወታደሮች ፥ 40.000 የጭነት እንስሳት ፥ 10.000 መኪናና ሞተር ብስክሌቶች አሉበት ። ይህ ክፍለ ጦር እ.ኤ.አ. 1935 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ በኛ አቆጣጠር በታህሳስ ወር 1928 ዓ.ም. የነበረው የጦር መሣሪያ ብዛት 2.003.670 የመድፍ ጥይት ፥ 291.980.270 የጠመንጃ ጥይት ፥ 785.440 የጅ ቦምብ በጠቅላላው 29.771 ቶን የሚመዝን የጥይት አይነት ነበረው ። ከኢትዮጵያ ጋር ያለው ጦርነት ተጀምሮ ውጊያው ሲፋፋም ይህ 1ኛ ክፍለ ጦር ኃይሉን አጠናክሮ 350.000 ወታደሮችና 90.000 መንገድ ሠሪዎች ከ70.000 እንስሶች ጋር ነበሩት ። ይህ ሁሉ ጦር ለራስ እምሩ ሠራዊት የተሰለፈ ነው ማለት ሳይሆን ጠቅላላ የክፍለ ጦሩን ኃይል ለመግለጽ ያህል ነው ።

የካቲት 21 ቀን 1928 ዓም በጀኔራል ማራቬኛ የሚመራው 20.000 ወታደሮች ያሉበት ጦር ከአክሱም ተነስቶ ወደ ሰለክላካ ጉዞ ጀመረ ። እስከ ማግስቱ ቀትር ድረስም በሰላም ተጉዞ ሰለክላካ ደረሰ ። ቀትር ላይ ስድስት ሰዓት ሲሆን ሰለክላካ ሸለቆ ውስጥ ተኩስ ተከፈተበት ። በሰለክላካ ሸለቆ የመሸገው የኢትዮጵያ ሠራዊት አልበገር ብሎ ጠንክሮ በመከላከሉ ውጊያው ለሊት ድረስ ቆየ ።ጀኔራል ዳንቴ ቦናይቲ ስለዚያች ዕለት ሁኔታ ለአንጂሎ ዴልቦካ እንዳጫወቱት «...ጀኔራል ማራቬኛ አሳሽ ቀዳሚ ጦር ቀድም አድርጎ ልኮ ቢሆን ኖሮ እንደዚያ

ዓይነቱ ጭንቅ ውስጥ እንገባም ነበር ። እንዲህ ባለማድረጉና እኛም ባለማወቅ ልክ ሽርሽር እንደሚሄድ ሰው ስንጓዝ በጫካው የተደበቁት ኢትዮጵያውያን ሳናስበው አንድ ጊዜ ከላያችን ላይ ወድቀው በመትረየስ ተኩስ ከፈቱብን ። አዲ ሃይማናል ኮረብታ ላይ የነበሩትም እየሮጡ ወረዱ ። መድፈኞቻችን ጥይት እስቲ ያጉርሱ ድረስ ሁላችንም ተኩስ ለመተኮስ ግራ ተጋባን ። የኢትዮጵያውያኖች መሣሪያ አሮጌ ቢሆንም ጥሩ ተኳሾች በመሆናቸው ብዙ ጉዳት አደረሱብን...» ብሏል ።

ኢትዮጵያውያኖቹ እንዲህ ዓይነቱን ሽብር በኢጣሊያ ሠራዊት መሀል ካስነሱ በኋላ አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ጥይት የተጫኑትን መኪናዎች ለመማረክ ይሽቀዳደሙ ጀመር ። ቢሆንም የኢጣሊያ ወታደሮች ተበራተው ተኩስ በመጀመራቸው የዚያን ዕለቱን ውጊያ ጀምበር ገላገላቸው ። ስለዚያች እለቷ ውጊያ ቶማሴሊ የቆሰለውን የኢጣሊያ መኮንን ሎዊጂ ባርዚኒን ስለሁኔታው ጠይቆት የሰጠውን መልስ በመጽሐፉ ጽፎታል ። «...ወደ ኢትዮጵያውያኖቹ የመትረየስ ጥይት እንዘራለን። ኢትዮጵያውያኖቹ ግን መትረየሳችንን ዝም ለማሰኘት እየተወረወሩ ከላዩ ላይ ይወድቁበታል። ...እደገኛ ተዋጊዎች ናቸው ። አንድ ጊዜ እንዳየሁት 15 በሚሆኑ ኢትዮጵያውያኖች መሀል በምብ ተጣለና አስሩን ገደላቸው ። የተረፉት አምስቱ በመሸሽ ፈንታ የደረሰውን አደጋ ጉዳይ ሳይሉት እየሮጡ መጥተው ከጦራችን ጋር ተደባለቁ ።...» ብሎ አጫውቶታል ።

የሁለቱንም ጦር ስሊቱ ስለገላገለው ሁለቱም ጦር ተፋጦ አደረ ። በማግሥቱ ጀኔራል ማራቪኛ በራዲዮ ባዶሊዮን ምክር ጠየቀ ። «....እስከሚቀጥለው ቀን ድረስ እንዳትዋጋ ብዬ መለስኩለት ።...» ይላል ባዶሊዮ ። ባዶሊዮ ይህን ትእዛዝ የሰጠው ሌላ ፕላን ለመለወጥ እንጂ የኢትዮጵያውያኖቹ ግፊት ጦርነቱን ፣ ሊያቆመው አይችልም ። በዚህም ምክንያት በማግሥቱም ማለት የካቲት 23 ቀን ኢጣሊያኖቹ የኢትዮጵያን ጦር በአይሮፕላን ጭምር ሲከላከሉ ዋሉ ። ከጥቁርና ከነጭ ወታደሮች የተውጣጣ ጦር ቆየፃ የተባለውን ኮረብታ ይዞ ለመመሸግ የኢጣሊያ ሠራዊት በተንዘበት ጊዜ ኢትዮጵያውያኖች ኮረብታውን ላለማስያዝ አራት ሰዓት ሙሉ ተዋጉ ። ባዶሊዮም በመጽሐፉ «...ከ1300 እስከ 1700 ሰዓት ድረስ ኢትዮጵያውያን በአውቶማቲክ መሣሪያ ጠንክረው ተዋጉን...» ሲል ጠቅሶታል ።

ኢትዮጵያውያን ድል ሳያደርጉም ድል ሳይሆኑም እንደተለመደው ጦርነቱን ምሽት ገላገለው ። ፓውል ጀንቲዞን ስለዚያች ዕለት እንደፃፈው «...ማርች 2 ማታ (በኛ የካቲት 23) ሁለተኛው ክፍለ ጦር ጥይቶችን ሲያሰላ በሁለት ቀን ውጊያ የተተኮሰው የመድፍ ጥይት አርባ ሺ ሆኖ ተገኘ ። በጠመንጃና በመትረየስ የተኮሱት ጥይቶች ደግሞ ስምንት ሚሊዮን ሆኑ ።....» ሲል ገልጾታል ። ይሄው ደራሲ ስለዚያ ቦታ ጦርነት ሲጽፍ«...ጥቂት የአበሻ ወታደሮች ተማርከው ነበር። እነሱም የጦራቸውን ወሬ እንዲናገሩ በአስተርጓሚ ሲጠየቁ እመጨረሻው ሰው ድረስ ኢትዮጵያውያን ይዋጋሉ ። እኛንም ብትለቁን ከጎዳችንን እስትንተራስ ድረስ እንዋጋለን ። ይሄ የሁላችን የኢትዮጵያውያን ቃል ነው ።...አሉ...» ብሏል ።


ፓውል ጀንቲዞን በመጽሐፉ ሌላ ገጽ ላይ «....እንደ ራስ እምሩ ሠራዊት የተዋጋ የለም ። በኢጣሊያኖችም ላይ ከባድ ጉዳት አድርሰዋል ። 63 መኰንንኖች ፣ 894 ኢጣሊያዊ ወታደሮች ገደሉ ። ከነሱም ከኢትዮጵያውያን በኩል አራት ሺ ያህል ሰው ሞቷል ወይም ቆስሏል ።....» ይላል ።

እስከ የካቲት 26 ቀን ድረስ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሰለከላካን ሳይለቅ ጠንክሮ ሲዋጋ ቆየ ። ይህን የኢትዮጵያውያኖችን አልበገርነት የተመለከተው ባዶሊዮ የኢጣሊያ አየር ኃይል ባለው ኃይሉ ሁሉ የኢትዮጵያን ጦር እንዲደበድብ አዘዘ ። በዚህም ትእዛዝ መሠረት የኢጣሊያ አየር ኃይል እስከ ተከዜ እስከ ፀለምቲ ድረስ


እያለፈ በመብረር የራስ እምሩን ጦር በቦምብና በመትረየስ ይደበድብ ጀመር ። በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ከአይሮፕላን የተጣለው ቦምብ ብቻ ስምንት ቶን የሚመዝን ነበር ። በዚህም ቢሆን የኢትዮጵያ ሠራዊት አልተበገረም ።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ቦታውን ሳይለቅ ጠንክሮ በመዋጋቱ የተከዜ ሸለቆና ጫካ እሳት በሚረጭ ቦምብ እንዲደበደብና የመርዝ ጋዝ እንዲረጭበት ባዶሊዮ አዘዘ። ከዚህ ትእዛዝ በኋላ ባንድ ጊዜ የተነሳው አየር ኃይል ብቻ 25.000 የመትረየስ ጥይት ተኩሶ ተመለሰ ። የተከዜ አካባቢም በሙሉ ሬሣ ብቻ ሆነ ። ራስ እምሩም ከሞተውና ከሸሸው ሠራዊት የተረፉዋቸውን 300 ወታደሮች ያህል ይዘው ሲሸሹ የኢጣሊያ አይሮፕላን ደርሶ መትረየስ ተኮሰባቸው ። እሳቸውም ከነሠራዊታቸው ጫካ ገብተው አመለጡ ። በዚያ በኩል የመጣው ጦርም ገስግሶ ጐንደርን ያዘ ።


---




ሽሬ ከተማ ።




የሽሬ አካባቢ በቦምብና በመርዝ ተቃጠለ ።



የተከዜ ወንዝ በአይሮፕላን መርዝ ተረጨበት ።



በሰለከላካ የተጓዘው የኢጣሊያ ጦር ።



የሽሬው ውጊያ ።



የሽሬው መድፈኛ ጥይት ሲያጎርስ ።

# ማይጨው

የኢትዮጵያ ጦር ከሠፈረበት ከማይጨው ሶስት ኪሎ ሜትር ርቆ መካን ከተ ባለው ቦታ የኢጣሊያ ጦር ጉድጓድ ምሶ መሽጓል ። ይህም የምሽግ ቦታ ማይ ጨውንና አካባቢውን ሁሉ ወለል አድርጐ ስለሚያሳይ ለቁጥጥር አመቺ ነው ። በስተቀኝ አምባ በሆር በተባለው ቦታ አልፒን የሚባለው የተራራ ወጪ ክፍለ ጦር ሠፍሯል ። በመሀል የማይጨውን ጦር የሚከላከል 2ኛው ክፍለ ጦር ሲኖር በስተግራ 1ኛው ክፍለ ጦር መሽጓል ። በጠቅላላውም አርባ ሺ የኢጣ ሊያ ወታደሮች ተሰልፈዋል ። ለዚህ ለቀዳሚው ጦር ደጀን እንዲሆኑ ሳባውላ ፣ አሲየታ ፣ እና ቴርዞ (3ኛ) ጃንወሪ የተባሉት ሶስት ዲቪገርኖች ከበላጉ እስከ አላጌ ድረስ ሠፍረዋል ።

ስለኢጣሊያ ምሽግ መጠናከር ቶማሴሊ ሲጽፍ«....የመጀመሪያው የማይጨው ምሽጋችን እንደሌላው ጊዜ በሽቦ አልታጠረም ። ፈንጂም ለመከላከያ አልቀበር ንም ። ጥሩ አድርገን የተማመነው በጥሩ ሁኔታ ቆፍረንና ገንብተን በግንድ ክምር ያበጀነውን ምሽጋችንን ነው ። .....ይህን ሁሉ ለማዘጋጀት የረዳንና ጊዜም ያገኘ ነው ኢትዮጵያውያኖች ጦርነቱን ለመጀመር ከጊዜ ጊዜ እየለዋወጡ በምክር ብቻ ጊዜውን ስላራዘሙልን ነው ።.....» ብሏል ።

ኰሎኔል ኮኖቫሎፍ የኢጣሊያን ጦር አሰላሎ ካወቀ በኋላ«... መጋቢት 12 ቀን 1928 ዓም ከንጉሡ ዘንድ ቀርቤ ባሁኑ ጊዜ የኢጣሊያ ጦር ገና በመዘጋጀት ላይ ስለሆነ አመቺ ጊዜ ነውና እንግጠም አልኳቸው ። ንጉሡም ማርች 24 ቀን (በኛ መጋቢት 15) እንገጥመዋለን አሉኝ ።....በማርች 24 ቀንም የኢጣሊያን ጦር አልገጠምንም ።...» ይልና ስለማርች 24 ቀን ሁኔታ ሲተነትን«...ማርች 24 ቀን ከሰዓት በኋላ ንጉሡ ግብር አደረጉ ። ግብሩ የተደረገበት ዋሻ አርባ ሜትር ያህል ርዝማኔ አለው ። ዋሻው በሙሉ ምንጣፍ ተነጥፎበታል ። በበራፉ ላይ ነጫጭ ሀር የለበሱ የሥራ ሚኒስቴር ሠራተኞች ቆመዋል ።...ንጉሡ ለጊዜው በተዘጋጀላቸው ዙፋን ላይ ተቀምጠዋል ። ራስ ካሣና ራስ ስዩም ከንጉሡ ጐን አሉ ። ከነሱም ዝቅ ብሎ ሌሎች ሹማምንት ተቀምጠዋል ።....እኔ ስገባ ግብሩ መበላት ተጀምሮ ነበር ። የተወደደውን ጥሬ ሥጋ የእልፍኝ አሽከሮች በየገበታው ያድላሉ ። ሌሎ ችም በየትናንሽ ኩባያ ጠጅ ይሰጣሉ ።....» ብሏል ።

መብልና መጠጡ (ግብሩ) ካለቀ በኋላ ንጉሡ ለተሰበሰበው ሠራዊት ንግግር አደረጉ ። በንግግራቸውም ለጦር መዘጋጀታቸውን ገልፀው«...ዛሬ ለሊት ይጀመ ራል ።..» አሉ ። የተሳከረው መኳንንትም ጊዜው አጠረብን እያለ ይናገር ጀመር ። መኳንንቱ ጊዜው አጠረብን ያለው አስቀድሞ ዝግጅት መኖሩ ስላልተነገረው አብዛኛው ሠራዊት በፊት ከነበረበት እያ ከተባለው ቦታ አልተነሳም ነበርና ነው። በዚህ ምክንያት አቅም ያንሰናል ብለው ተቃወሙ ። ስለዚህ ነገርም ባርከር ሲተች «....መሳሪያ የያዘው ወታደር አልደረሰም ። ከማይጨውም ያለው ወታደር ቢሆን ቀደም ብሎ ስላልተነገረው ለውጊያ አልተዘጋጀም ። ስለዚህ ነው ውጊያው ለሌላ ቀን ይተላለፍ ብለው ያመለከቱት ።...» ይላል ።

የጦርነቱ መጀመሪያ ለመጋቢት 15 ቀን መሆኑ ቀርቶ ለመጋቢት 19 ቀን እንዲሆን ተወሰነ ። መጋቢት 19 ቀን ደረሰ ። ኮኖቫሎፍ እንደጻፈው«...በዚያን ቀን ንጉሡ የጦር አዛዦችን ሰብስበው «...ውጊያውን ትገጥማላችሁ ። እኔም ከዚህ

ሆኜ በመድፍና በሞርታር ድጋፍና ሽፋን እሰጣችኋለሁ ...እሉን ፡...» ይላል ፡ ጦሩም በሶስት ክፍል ተከፍሎ ራስ ካሣ ፥ ራስ ሥዩምና ራስ ጌታቸው እንዲመሩት ተደረገ ፡ ስለዚህም የጦር አከፋፈል አንጂሎ ዴል ቦካ ሲተችዛ...ራስ ካሣና ራስ ስዩም ይዋጋሉ ብሎ ማሰቡ ሞኝነት ነበር ፡ ሁለቱም የኢጣሊያን ጦር ቀምሰው ሸሽ ተው የተመለሱ ናቸው ፡ ከተከበሩ ሰዎች የተወለዱ የተከበሩ ሰዎች በመሆናቸው ብቻ የጦር አዛዥነቱ ቦታ ተሰጣቸው ፡...ሌሎቹም የጦር አዛዦች ቢሆኑ ያው ናቸው ፡ ደጃች መንገሻ ይልማ ፥ ሊጋባ ጣሰው ፥ ራስ ከበደ መንገሻ ፥ ደጃች ለጥ ይበሉ ፥ ደጃች ወንድይራድ ሁሉ የጦር አዛዦች ተብለዋል ፡ ግን ጦርነቱ ሲጀመር ከጦርነቱ ቦታ 24 ሰዓት አልቆዩም ፥...» ይላል ፡

ለመጋቢት 19 ቀን የተወሰነው ውጊያ የጦሩ ዝግጅት አልተሟላም ተብሎ ለ21 ተቀጠረ ፡ ለመጋቢት 21 መቀጠሩን የኢትዮጵያ ወታደር ሳይሰማ ባዶሊዮ ሰማ ፡ ባዶሊዮ ይህን ቀጠሮ ሊያውቅ የቻለው ንጉሡ ነገሥቱ ለእቴጌይቱ በራዲዮ «...ቅዳሜ ወይም ሰኞ እንገጥማለን...» ብለው ካሳለፉት መልእክት ነው ፡ባዶሊዮ ይህን ካወቀ በኋላ ጦሩን ለቅዳሜ ውጊያ አዘጋጀው ፡ ቅዳሜ ጧት መኳንንቱ ተሰ ብስበ አልተዘጋጀንምና የውጊያው ቀን ይተላለፍልን ብለው አመለከቱ ፡ ኰናኛ ሎፍ ስለዚያች ቅዳሜ እለት ሲገልጽ«....እንደጦር አማካሪነቴ ተጠርቼ ከንጉሡ ዘንድ ገባሁ ፡ በዚያም ቦታ ለመናገርም ሆነ ለማድመጥ ፈጽሞ የማይቻል ነው፡ ከውጭ ፥ ወታደሩ ለብዙ ጊዜ እየጠበቀ የተጉላላ በመሆኑ ተሰላችቶ ጥይቱን ወደ ሰማይ ይተኩሳል ፡ ከነዚህም ጥቂቶቹ እየተያዙ ታስረዋል ፡ አንዳንዶቹም ለመቀ ጣጫ በአደባባይ ተገርፈዋል ፡ ይህ ሁሉ ቅጣት ወታደሩን ፀጥ ሊያደርገው አል ቻለም ፡ ...” ይላል ፡ በዚያ ቀን በተደረገው ምክር ውጊያው ለመጋቢት 23 ቀን እንዲሆን ተቀጠረ ፡

“...ኢጣሊያ ምሽጉን በሚገባ አጠናክሮ ከሩቅም በሽቦ ማጠሩን ንጉሡ በመነጥር ያዩት ሰኞ ዕለት ነው ፡ ጫማ የሌለው የኢትዮጵያ ወታደር ያን ሽቦ እን ዴት ያልፈዋል ?... ሰኞ ከሰዓት በኋላ ውጊያው የሚመራው በራስ ካሣ ፥ በራስ ስዩምና በራስ ጌታቸው መሆኑ ባዋጅ ተነገረ ፡... እነዚህ ሰዎች ጦሩን ሊመሩ አይችሉም ፡ ግን በፊውዳል ሥርዓት መሠረት ጦር የመምራት መብት ስላላቸው ብቻ ተሾሙ ፡ ሌሎች ወጣቶች የጦርነት ሞያ ትምህርት ያላቸው ምርጥ መኰ ንኖች ነበሩ ፡ በንጉሡ አስተያየት እነኚያን መኰንኖች መሾም ፥ የመሳፍንትን ክብር መንካት ሆነባቸው ፡... የጦርነቱ ፕላን የተዘጋጀው በንጉሡ ብቻ ነው ፡...ፕላ ኑም እንደጥንቱ ወረራ የተዘጋጀ በመሆኑ ይሄው ፕላን ለመኳንንቱ ቀረበ ፡ መኳ ንንቱም ‘ብትክክል እንዶ አድዋ ድል እናደርጋለን’ ብለው በፕላኑ ተማመኑ ፡...” በማለት ባርክር ይተቻል ፡

መጋቢት 23 ቀን ደረሰ ፡ እንደተለመደው መኳንንቱ መጋቢት 21 ቀን ማታ ተሰበሰበ “...የጊዮርጊስ ዕለት መጋጠሙ ጥሩ ስላይደለ ጊዜው ይተላለፍ ብለው ጠየ ቁ...” ይላል አንጂሎ ዴል ቦካ ፡ አንድ ስሙን ላገኝ ያልቻልኩት የሃማሴን ተወላጅ በክብር ዘበኛ ጦር ውስጥ ነበር ፡ ይህ ሰው ቀድሞ በኢጣሊያ ወታደር ውስጥ ተቀ ጥሮ ሲያገለግል ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ስትከፍት ወንድሞቼን አልወጋም ብሎ ከኢጣሊያ ጦር ከድቶ ወደ ኢትዮጵያ ጦር የገባ ነው ፡ ይህ አገሩን የሚወድ የሐማሴን ተወላጅ በቀጠሮው መብዛት ምክንያት ተናዶ ፡ የመጨረሻ የተባለው ቀጠሮ በመፍረሱም የባሰ ተበሳጨ ፡

ይህ ጀግና የሐማሴን ተወላጅ ሌሊት ከኢትዮጵያውያን ሠፈር ጠፍቶ ወደ ኢጣሊያኖች ሠፈር ሄደ ፡ በዚያም ከጀኔራል ኔግሪ (NEGRI) ዘንድ አቅርቡኝ ብሎ ከቀረበ በኋላ ባለፈው የመክዳት ስህተቱ ተፀፅቶና ከኢትዮጵያ ወታደር ጋር መኖር እንደማይቻል ነግሮ “...አሁን የመጣሁት ዛሬ ሌሊት ኢትዮጵያውያን በድ ንገት ሊወሩዋችሁ ተዘጋጅተዋል ፡ ያሳደገኝ የኢጣሊያ መንግሥት በድንገት ተወ

ርር እንዲዋረድ ስለማልፈልግ ይህን ልገልጽላችሁ ነውና ተዘጋጁ ።...” አላቸው ። ቶማሲሊና ማቴውስ በየመጽሐፎቻቸው ስለዚያ ሐማሴን ታሪክ በሰፊው ጽፈዋል ። “...ብዙም አትጨነቁ አለ ።...” ይላሉ ታሪክ ፀሐፊዎቹ “...እኔ እንደነበርኩ መስዬ ወደ ኢትዮጵያ ጦር ሄጄ እደባለቃለሁ ። የኢትዮጵያ ጦር ሌሊት በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ለየት ብዬ ከመሃል ቦታ ሆኜ ሁለት የሽጉጥ ጥይት ተኩሼ ምልክት እሰጣችኋለሁ ። እኔ የምሰጣችሁን ምልክት መስማታችሁንና መዘጋጀታችሁንም እንዳውቅ ቀይ ርችት ተኩሱልኝ ብሎ ሌሊቱን ከኢጣሊያኖቹ ሠፈር ወጥቶ ወደ ኢትዮጵያውያኖች ሠፈር ሄደ ።

“ከኢትዮጵያውያን ጦር ሠፈርም ሌሊቱን ገብቶ ... የኢጣሊያን ጦር ሠፈር ሰልዬ መጣሁ ። ዛሬ ሌሊት ሳይታሰብ በድንገት ሊገጥሙን ዝግጅታቸውን ጨርሰው ተሰልፈዋልና ታጠቁ ብሎ የተኛውን ሁሉ ቀስቅሶ ከጦር መሪዎቹም ዘንድ ቀርቦ ሲጠየቅ ያንኑ ቃል ተናገሮ .... እኔ ከናንተ ለየት ብዬ ወደ ኢጣሊያ ምሽግ ተጠግቼ ከረባዳው እሆናለሁ ። የኢጣሊያ ጦር መንቀሳቀሱንም እንዳየሁ ሁለት የሽጉጥ ጥይት ተኩሼ ምልክት እሰጣችኋለሁ ። የኢጣሊያ ጦርም ወታደሩን ከዳር እስከ ዳር ለመቀስቀስ ቀይ ርችት ይተኩሳልና በዚህ ምልክት ተጠቀሙ ብሎ ነገረና የሁለቱም ወገን ጦር ሌሊቱን በሚገባ ተዘጋጀ ።....” ይላሉ ሁለቱ ታሪክ ፀሐፊዎች ።

ማቲውስ እንደሚገልፁት “...ያ የሐማሴን ተወላጅ ከሌሊቱ 0545 ሰዓት ሲሆን ከመሀል ቦታ ሆኖ ሁለት ጥይት ተኰሰ ። ኢጣሊያኖቹም የምልክት ተኩስህን ሰምተናል ለሚለው መልስ ሁለት ቀይ ርችት ተኩሰው ገለፁለት ። ኢትዮጵያውያኖቹም ሐማሴኑ በነገራቸው መሠረት የኢጣሊያ ጦር በሙሉ ለመንቀሳቀሱ የርችቱን ተኩስ አዩ ።....” እንዲህ አድርጎም በቀጠሮው ብዛት የተናደደው ሐማሴን የማይጨውን ጦር ማጋጠም ቻለ ።

ተኩሱ ለመጋቢት 22 አጥቢያ ከሌሊቱ ለ12 ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን የተከፈተው በ2ኛው ክፍለ ጦር በፑስቴሪያ አቅጣጫ ነበር ። ውጊያው እንደተጀመረ ኢትዮጵያውያን አጠቁ ። የኢጣሊያ ሠራዊትም ወደኋላው ማፈግፈግ ጀመረ ። ኢትዮጵያውያንም እያባረሩ የኢጣሊያ ሠራዊት ከምሽጉ ሲገባ ኢትዮጵያውያን ከወጥመድ ገቡ “....የዚያን ዕለቱ ውጊያ በጣም ከበደብን ። የ24ኛው ብርጌድ አዛዥ ኰሎኔል ሮሣ ተመትቶ ሲወድቅ የመድፍ እርዳታ መጠየቂያውን ርችት አስተኩሶ ሞተ ። ከኰሎኔል ሮሣ ሞት ጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ብሎ የ7ኛው ብርጌድ አዛዥ በጥይት ክፉኛ ተመትቶ ወድቋል ። መትረየስ ተኳሻችን እምሳ አለቃም ተመትቶ ሲወድቅ አጠገቡ የነበረ የአልፒን ወታደር በቦታው ተተክቶ መትረየሱን ገና ከመያዙ በስከንድ ጊዜ ውስጥ ተገደለ ። እዚያው መትረየሱ አጠገብ የነበረ ሌላ የአልፒን ወታደር እየተኰሰ ወደ ምሽግ ሲሸሽ ራሱና ትከሻው ላይ ክፉኛ ተመትቶ ወደቀ ።...” እያለ ቶማሲሊ የጦርነቱን ዝርዝር ሁኔታ ጽፏል ።

ኡን ቪቶሬ ዴላ ሲቪላዜሽን የተባለው መጽሐፍም “...ከሐረርጌ የመጡ የጦር ትምህርት የተማሩ ወጣት መድፈኞች የኢጣሊያ 8ኛ መድፈኛ ባታሊዮንን ወታደሩን ብቻ ሳይሆን መ ኰንኖችን ጭምር ፈጁዋቸው ።..... ኢትዮጵያውያን ግብር በማግባትና ፀሎት ይዘው በቀጠሮ ብዛት ባይቆዩ ኖሮ ከዚያ ቦታ የኢጣሊያ ሠራዊት ተርፎ አይመለስም ነበር ። የኢትዮጵያ ጦር አዛዦች ግብር እየበሉ ፀሎት ፀልዩ እያሉ በሚሉበት ጊዜ ኢጣሊያኖች ጥሩ ምሽግና ሰውን በቁመቱ ሙሉ የሚከልል ጉድባ አዘጋጁ ። ጦርነቱ ተጀምሮ አበሾቹ ባጠቁ ጊዜ ኢጣሊያኖችን ከእልልቂት ያዳናቸው ከውጊያቸው ይልቅ ምሽጋቸው ነው ...” በማለት ይተቻል ።

የኢትዮጵያ ጦር አማካሪ የነበረው ኮኖቫሎፍ ደግሞ “.....የኛ መድፈኞች ስለ ፕላኑም ሆነ ስለሌላው የሚያውቁት ነገር ስለሌለ ብዙ ጊዜ የሚተኩሱት የመድፍ ጥይት ጠላት ላይ ሳይሆን ጠላት ወደሌለበት አቅጣጫ ነበር ። አንዳንዶም

በራሳቸው ወገን ላይ ይተኩሱበት ነበር ። ለምን እንዲህ እንደሚሆንም ንጉሡን ብጠይቅ 'የኛ ሰው የመድፍ ድምፅ ሲሰማ ጀግንነት ይሰማዋል ። ሞራሉም ይበረ ታል' አሉኝ ።……" በማለት ጽፏል ።

በተገኘው የዕለት ድል የተደሰተው የኢትዮጵያ ሠራዊት ግዳይ ለመጣል ወደ ኋላ እየተመለሰ ተቀምጦ ከሚጠብቀው የጦር አለቃው ፊት ይፎክር ጀመር ። በዚህ ጊዜ የኢጣሊያ ጦር ፋታ አግኝቶ መሰባሰብ ጀመረ ። የደጀን ጦሩም ደረሰለት ። ይህንን የግዳይ መቀበሉን ጉዳይ የኡን ቪቶሪ ዱላ ሲቪሳዚሽን ደራሲ ለምን እንዲህ እንደሚሆን ንጉሡን ጠይቆ ነበር ። "…እየሀ አሉኝ ንጉሡ…" ይላ ል። "…እንደ አገራችን ባህል መሠረት በጦርነት ጊዜ ወታደሩ ግዳይ መጣል ስላለ በት እኔ ወዳለሁበት ወደ ዋናው ጦር ሠፈር ወታደሩ ይመጣል ። ሲመጣም የማ ረከውን መሣሪያ በትከሻው እየተሸከመና እየሸለለ ነው ። ከኔም ዘንድ ደርሰው ሲፎክሩ ወኔያቸውን ለማነቃቃት የግል መትረየስ ተኳሾቼን መትረየስ እንዲተኩ ሱላቸው አዝዣለሁ ። …. አሉኝ…" ይላል ።

የደጀኑ የኢጣሊያ ጦር እስኪደርስ ድረስ የጥቁር ወታደሮች ብርጌድ አዛዥ የሆነው ፒርዚዮ ቢሮሊ ምሽግ የገባ ወታደሩን ሰብስቦ "………አበሾቹ የሽቦ አጥ ሩን አልፈው ከምሽግ ገብተው ይፈጁናል ብላችሁ አታስቡ ። አሁን እናንተ ማድ ረግ ያለባችሁ አንዳንድ ጥይት እየተኮሳችሁ ጥይታቸውን አስጨርሷቸው ።….." ብሎ አዘዘ ። እንዳለውም ኢትዮጵያውያን ላንዳንድ ተኩስ መልስ ለመስጠት በማለት በብዛት ይተኩሱ ጀመር ። ምትክ የሌለው የወገባቸው ጥይት እንዳለቀም ወደኋላ ማፈግፈግ ጀመሩ ። ኮኖቫሎፍም "… ጥንክር የሆኑ 900 ሰዎች ያህል በጀግን ነት ተዋጉ። የወገባቸው ጥይት ሲያልቅ ምንም ማድረግ አይቻልምና እኒሱም እንደ ሌሎቹ ወደ ኋላ ተመለሱ ።….." ብሏል ። ይህ ሁሉ የሆነው ገና በማለዳ ነበር ።

ረፋዱ ገደማ ላይ ደጀኑ የኢጣሊያ ጦር ደረሰ ። የኢጣሊያ አይሮፕላኖችም ከጧቱ ሁለት ሰዓት የተጀመረ የቦምብ ድብደባቸውን አጠናከሩ ። የጦር ትምህርት የተማሩት የሆለታ ምሩቃን ክብር ዘበኞች ወደፊት ገፉ ። ባዶሊዮ እንደሚገልፀው "…የአየር ኃይሉ ፣ ማጥቃት እንደጀመረ ጠቅላላው የክብር ዘበኛ ወታደር ሶስት ሰዓት ሲሆን በደጀን ተኳሾች ተከልሎ ሊያጠቃን መጣ ። በጥሩ የጦርነት ትምህርት የሰለጠኑ መሆናቸውን የሚያስመሰክር ውጊያ ተዋጉን ።…. 10ኛውን ባታሊዮንም በመግደልና በማቁሰል ጨረሱት ። እየፎከሩ አሻፈረኝ የሚል ዘፈን እየዘፈኑ ገፉ ። …ያሉበትንም ምድር በጥሩ የጦርነት ታክቲክ ተጠቀሙበት ። ከአደጋ ተጠንቅቀው አደጋ መጣል የሚያስችል ትምህርት የተማሩ መሆናቸውንም አወቅሁ…" ሲል መስክሮላቸዋል ።

ከጧቱ በአምስት ሰዓት ላይ 10ኛው ባታሊዮን ባዶ በመሆኑ የባታሊዮኑ አዛዥ ሌተና ኰሎኔል ዙሬቲ ለጠቅላይ ጦር ሰፈሩ "… ከባድ የጠላት ኃይል ገጥ ሞናል ።…. ይህን እኛ ያለንበትን ቦታ ሣር ቤቶች ካሉበት አካባቢ ደህና አድር ጋችሁ በመድፍ ደብድቡልን ።…." ሲል አመለከተ ። ይህን ባመለከተ ከጥቂት ደቂ ቃዎች በኋላ የ10ኛው ባታሊዮን አዛዥ ራሱ ኰሎኔል ዙሬቲ እና ኰሎኔል ሩጀሮ ተገደሉ ። በዚያ ቦታ ከዳኑት ጥቂት መኰንኖች ውስጥ የኒኦፖሊታኑ መኰንን ራፋ ኤል ታራንቲኒ በነሱ ቦታ ተተክቶ ማዘዝ ጀመረ ። በቦታው ተተክቶ ማዘዝ እንደ ጀመረም ለ2ኛው ክፍለ ጦር አዛዥ ለጀኔራል ዳልማዞ ( Dalmazzo ) ባስተላለ ፈው መልዕክት "…አሁን ከዚህ ቦታ የሚታኰሰው የቆሰለ ሠራዊት ብቻ ነው ። በቅርብ ጊዜ ሁላችንም እንሞታለን ። እስከንሞት ድረስ ግን መታኮሳችንን እንቀጥ ላለን ።…" ሲል ማመልከቱን ቶማሲሊ ጽፎታል ። የክፍለ ጦሩ አዛዥ ጀኔራል ዳል ማዞ ሠራዊቱ ጠመንጃውን ይዞ ወደፊት እንዲገፋ አዝዞ ያዋጋ ጀመር ።

የክብር ዘበኛ ወታደሮችም የኢጣሊያን ምሽግ ሰብረው ሊገቡ ሲሉ ከምሽጉ ውስጥ ያሉ ኢጣሊያኖች የጅ ቦምብ በብዛት እየጣሉ መለሱዋቸው ። ብዙ

ውም ከዚያች ቦታ ተሰዋ ። "...በዚያች ዕለት ያዳነን የጅ ቦምባችንና የቅርብ መትረየሳችን ነው ።...." በማለትም ባዶሊዮ መስክሯል ። ጦርነቱን ጀምበርም፣ እሌቂትም ገላገለው ። የኢትዮጵያ ሠራዊት እስከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተዋግቶ በትዕዛዝ ተመለሰ ።

የአፍሪካው የኢጣሊያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ማረሻል ባዶሊዮ ቀኑ ሲጨልም ጦርነቱ ስለቆመ ኢትዮጵያውያን ተዘጋጅተው በነጋታው እንደሚገጥሙ አስቦ ፕላን በማውጣት ላይ ሳለ ንጉሠ ነገሥቱ ለእቴጌይቱ ማታውኑ ያስተላለፉት የራዲዮ መልዕክት ተጠልፎ ደረሰው ። መልእክቱም ".......ከሌሊቱ 11 ሰዓት ጀምረን እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ድረስ ሠራዊታችን ከባዱን የኢጣሊያን ጦር ሲያጠቃ ቆየ ። በጀግንነትም ተዋጋ ። በውጊያውም ውስጥ እኛ ራሳችን ተካፋይ ነበርን ። ከመኳንንቶቻችንና ከታማኝ ወታደሮቻችን መሀል የሞቱም የቆሰሉም አሉ ። በኛ ሠራዊት ላይ የደረሰው ጉዳት ከባድ ነው ። ጠላትም ቢሆን ተጐድቷል ። የክብር ዘበኞች በአስደናቂ ጀግንነት ተዋግተዋል ። .....ሠራዊታችን እንደኤሮፓውያን የጦር ትምህርት ባለመማሩ ሊፈታ ቻለ ።...." የሚል ነበር ። ባዶሊዮ ይህን መልእክት ከሰማ በኋላ የኢትዮጵያ ሠራዊት ድል መሆኑን አረጋገጠ ።

በማግሥቱ መጋቢት 23 ቀን ከሞት የተረፈው የኢትዮጵያ ጦር ተጠረቃቅሞ ሊዋጋ ነበር ። በዚያ ዕለት ከባድ ዝናብ በመጣሉና ቦታውን ሁሉ ደመና ስለሸፈነው ንጉሠ ነገሥቱ ተስፋ የሌለው መሆኑን አውቀው ጦሩ እንዲመለስ አዘው የደሴ ጉዞ ተጀመረ ።

"....ከልካዮች ..." ይላል ኮናቫሎፍ የመጋቢት 23 ቀኑን ሁኔታ ሲገልጽ ። "ከልካዮች ሰው ወደ ንጉሡ ዋሻ እንዳይጠጋ ይከላከላሉ ። በግራም በቀኝም በአርጩሜ ይደባደባሉ ። ንጉሡም 'ምን ዓይነት የተዋረደ የሥነ ሥርዓት እጦት ነው? ከዋሻው ወጥተንስ እንዴት ማዘዝ ይቻላል?' አሉኝና ግራና ቀኝ እያዩ 'ፊታውራሪ ተፈሪ! የት ነው? የለም እንዴ? ቶሎ ፈልጋችሁ አምጡልኝ' አሉ ። ይህም አስታ ጉራዴውን መዞ እንደያዘ መጣ ። ንጉሡም በእጃቸው እያመለከቱ 'ትመለከታለህ ያን ደን የለበሰ ቦታ? በፍጥነት ሰዎችህን ይዘህ ሂደህ ያን ቦታ ያዝና ፈረንጆች እንዳይዙት ተጠባበቅ' አሉት ። ፊታውራሪው እጅ ነስቶ ወጣ ። ከሁለት ሰዓት በኋላ እዚያው እምሽጋችን ውስጥ ፊታውራሪው ከሰዎቹ ጋር ሲጫጫህ አገኘሁት ። እንደምንም ብሎ አምሳ ወታደሮች ላከ ። እሱ ግን እዚያው ከንጉሡ አጠገብ ቀረ ።..." በማለት የዕለቱን ስነ ሥርዓት መበላሸት ያብራራል ።

ሴም በመጽሐፉ ስለ አንድ ኢትዮጵያዊ ምርኮኛ ጽፏል ። "....አንድ የአበሻ ወታደር ተማረከና በአስተርጓሚ እንጠይቀው ጀመር ። ይህ ሰው ክፉኛ ቆስሎ ስለነበር እንደማይቆይ አውቀታል ። ምን ነበርክ አልነው ።

"የሺ አዛዥ (ሻለቃ) ነኝ ።"

"ለምን ከዚያ ከዋሻችን ውስጥ ገብተህ አትተኛም? ኢጣሊያኖች እኮ እስረኛ አንገድልም ።"

"ተኝቼ ሳይሆን በእግሬ ቆሜ መሞትን እመርጣለሁ ።"

"እንዲህ ማለትህ የጀግንነት መሰለህ?"

"ከሁለት ቀን በፊት እኛ አበሾች ተማምለናል ። የተማማልነውም ድል እናደርጋለን፣ ካልሆነም እንሞታለን ብለን ነው ። አሁን አላሸነፍንም ። ስለዚህ መሞት አለብኝ ። ተመልከት እዚያ ማዶ የወደቀውን ሬሳ ብሎ አሳየኝና እኔም እንደነሱ ተራዬን ነው የምጠብቀው አለ ።......"

በማይጨው ያለቀውን የኢትዮጵያን ሠራዊት ታሪክ ፀሐፊዎች በትክክል አይጽፉትም ። ኮናቫሎፍ አንድ ሺ ሰው ነው ሲል ቶማሴሊ ደግሞ 5.000 ነው ይለ

ዋል። ማርሻል ባዶሊዮ ደግሞ ስምንት ሺ ያደርሰዋል። በኢጣሊያኖች በኩል ኢጣሊያኖች እንደገለፁት 68 መኰንኖች ፣ 332 ነጭ ወታደሮችና 873 የቅኝ ግዛት ወታደሮች ሞተዋል ።

በማይጨው ጦርነት ሰባ አይሮፕላኖች ተካፋይ ሆነው ከነዚሁ ውስጥ 36 አይሮፕላኖች ተመትተው መውደቃቸውን ኢጣሊያኖቹ አምነዋል ። ተመትተው ከወደቁትም መሀል አንዱ የሙሶሊኒ ልጅ ቪቶሪዮ ሙሶሊኒ የሚነዳው ነበር ። እነኚህም ሰባ አይሮፕላኖች በመመላለስ በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ 34 ቶን የሚመዝን ቦምብና የመርዝ ጋዝ ጥለዋል ። በሌላው የኢጣሊያ መግለጫ በኩል 61.200 የመትረየስ ጥይት መተኰሱን ኢጣሊያውያን ጽፈዋል ።

ባዶሊዮም ለሙሶሊኒ ባሳለፈው ቴሌግራም "....በኢትዮጵያ ያለው ጦርነት አለቀ ። በማይጨው የተዋጋን የኢትዮጵያ ጦር ከጥቂት ወታደሮች በቀር የተረፈ የለም ።...." አለ ።

———O———

# የአሸንጌው እልቂት

መጋቢት 23 ቀን 1928 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ወታደር እህል ከቀመሰ 36 ሰዓት አልፎታል ። ተጉላልቷል ። ደክሟል ። አሁንም ቢሆን የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ከማ ይጨው ጦርነት የተረፈውን እየተከታተሉ በቦምብ ይደበድቡታል ። ያ የደከመና የተጉላላ ሠራዊት ወደ አሸንጌና ወደኮረም እንዲሄድ ታዘዘ ። ራስ ሥዩምም ሠራ ዊታቸውን ይዘው ወደ መቀሌ እንዲጠጉና ኢጣሊያን እንዲወጉ ታዘዙ ።

መጋቢት 25 ቀን ከንጉሡ ጋር የነበረው ሠራዊት ወደ አሸንጌ ጉዞውን ጀመረ። ይህ ሠራዊት ጥቂት መድፎች ይኑሩት እንጂ አብዛኛው ሕዝብ ቁስለኛ ነበር ። ይህን በመርዝ ተቃጥሎ የሚመለሰውን ሠራዊት የጐዳው የጠላት ጦር ብቻ ሳይ ሆን በኢጣሊያ ገንዘብ ተታለው የሸፈቱ ያገር ውስጥ ሽፍቶችም ጭምር ነበሩ ። ይህ የደከመ ሠራዊት እየተንገላታ መጋቢት 26 ቀን አሸንጌ ደረሰ ። አሸንጌ ኮረ ብታም ሆነ ደን የሌለበት ገላጣ ቦታ በመሆኑ ሠራዊቱ ያን ሥፍራ ቀን ለማለፍ ፈርቶ በደን ውስጥ ተሸሽጐ ቀኑን አሳለፈ ። የሠራዊቱ እሳብ ያን መከላከያ የሌ ለውን ሜዳ በለሊት ለማለፍ ነበር ።

ሠራዊቱ ደን ውስጥ ተሸሽጐ ባለበት ጊዜ የኢጣሊያ አይሮፕላኖች መጥተው ወረቀት በተኑ ። የተበተነው ወረቀትም«.... እኛ የምንፈልገው ንጉሡን ነው እንጂ እናንተን ወታደሮችን አይደለም ። ከእናንተም ጋር ጠብ ስለሌለን ማታ ማታ እርፋችሁ እየተኛችሁ ቀን ቀን በብርሃን በሰላም መንገዝ ትችላላችሁ ። እንነካችሁም ....» የሚል ነበር ። ይህን ከኢጣሊያ የተበተነ የሰላም ወረቀት ያየው የኢትዮጵያ ሠራዊት ከተሸሸገበት ደን እየወጣ ጉዞ ጀመረ ።

ሠራዊቱ ከጫካው ወጥቶ ከሜዳው ሲደርስ የአይሮፕላን ማጉረምረም ሰማ ። ወዲያውንም አይሮፕላኖቹ ደርሰው ቦምብ ይጥሉበት ጀመር ። ቶማሲሊ እንደሚገልፀው «...ለመጀመሪያ ጊዜ ከተጣሉት ቦምቦች አምስቱ አልፈነዱም ።...ሠራዊቱ የሚ ጓዝበትን የምዕራብ አቅጣጫውን ትቶ ወደ ምሥራቅ ሸሸ ። አላወቁም እንጂ በም ሥራቅ አቅጣጫ ሠራዊቱን እየተከታተለ እንዲፈጅ የታዘዘው 1ኛው ክፍለ ጦር በመምጣት ላይ ነበር ።...» ብሏል ።

በሜዳው ላይ በተበተኑት ሴቶች ፣ ቁስለኞች ፣ ስንቅ በጫኑ ከብቶች ላይ የዚ ያን ዕለት 73 ቶን የሚመዝን ቦምብና የመርዝ ጋዝ ተጣለ ። መትረየስ ተኳሽ አይ ሮፕላኖችም አስር ሜትር ድረስ ዝቅ እያሉ በመትረየስ ይፈጁት ነበር ። ኢትዮጵ ያውያኖችም በዚያ ቦታ ከሰማይ ጠላታቸው ጋር በሚያስደንቅ ጀግንነት ተዋጉ ። በካፒቴን ፋብሪ የሚነዳውን አይሮፕላን ለመጀመሪያ ጊዜ ከጣሉም በኋላ ይቀናቸው ጀመር ። ያን የደከመ ሕዝብ ለመጨረስ 150 አይሮፕላኖች እየተመላለሱ እንዲደ በድቡት ታዘው ነበር ። ከእነዚህ መሀል ኢትዮጵያውያኖቹ 28 አይሮፕላኖች መጣ ላቸውን ኢጣሊያኖቹ አምነዋል ።

የአሸንጌው እልቂት እንዴት ነበር? ከራሳቸው ከኢጣሊያኖቹ እንስማው ። በአ ይሮፕላን አብራሪነት ይዋጋ የነበረው አሌሳንድሮ-ፓቮሊኒ የተባለ የኢጣሊያ ፓይ ለት የተናገረው ዴስፔራታ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ተገልጿል ። እንዲህ ይላል። «....በጦርነት ውስጥ ገብቶ መዋጋት ያስፈራል ። ያሰጋልም ። ከሩቅ ሰማይ ላይ ሆኖ ቦምብ እየጣሉ መዋጋትም ብዙ ሬዛ አያሳይም ። በሰማይ መንገዳችን ምንም ተከላካይ ወይም መካች ፣ ከመሬትም ምንም አስጊ ነገር ስላልነበረ ዝቅ እያልን እንበር ነበር ። አሸንጌ ባለው በኢትዮጵያ ጦር ላይ ከመሬት አስር ሜትር ከፍታ ድረስ ዝቅ ብለን ሠራዊቱን በመትረየስ እንፈጀው ነበር ። በቦምብ ስለምንደበድ በውም ያ ትውልድ ፈጽሞ ማለቁን ተረዳን ። የኢትዮጵያ ሠራዊት የረጨንበትን

የመርዙን ጋዝ ለመታጠብ ከአሸንጌ ሐይቅ ዙሪያ ከቦ እንኘነው ። አይሮፕላኖቻ ችንም ዝቅ ብለው በመትረየስ ተኩስ ያደረሱበት እልቂት የማይረሳኝ ነው ።...»

ማርሴል ግሪውሊም በመጽሐፉ«....ከማይጨው ጦርነት የተረፈው የአበሻ ሠራዊት አሸንጌ ላይ ተሰበሰበ ። አይሮፕላኖቹ ከአሸንጌ ሐደው በዚያ ለተሰበሰበው የኢትዮጵያ ወታደር ወረቀት በተኑ ።....ይህን ወረቀት ያነበበ የኢትዮጵያ ሠራ ዊት በብዛት ወጥቶ ከሜዳ ላይ በደረሰ ጊዜ 150 የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ደርሰው በቦምብ ደበደቡት ። በመትረየስም ፈጁት። አንዳንድ በየጥጋቱ እየተደበቀ የቀረ የኢትዮጵያ ሠራዊት እንዳለ በማለትም የመርዝ ጋዝ ተረጨበት ። ሠራዊቱ እንደ ቅጠል ረገፈ...» ይላል ።

ያ ጀግና ሕዝብ ዘመናዊ መሣሪያ በማጣቱ ብቻ ዘመናዊ መሣሪያ ለያዘው ጠላቱ ማላገጫ ሆነ ። አይሮፕላን ነጂው የሙሶሊኒ ልጅ ቪቶሪዮ ሙሶሊኒ በመጽ ሐፉ«...ተኩሼ ኢላማዬን ሳልመታ ስቀር በጣም እበሳጫለሁ ።...በበረራዬ ላይ ሁልጊዜ ትዝ የሚለኝና የማስበው በአሜሪካውያን ፊልም ውስጥ ያየሁት ነገር ነው ።...ከአይሮፕላኑ ላይ ቦምብ እጥልና የጣልኳቸው ቦምቦች የሚያስነሱት የቃ ጠሎ እሳት ሰማይ ድረስ እየተኸመለመለ ሲመጣ ደስ ይለኛል ። አንዳንዴም በየ ማንደሩ ላይ ቦምብ ስጥል እንኚያ ከጭቃና ከሣር የተሠሩ የአበሻ ጐጆዎች እንደ ምኞቴ ተሳክተው በቃጠሎዋቸው ብዛት አያስደስቱኝም ።...» ይላል ። እያስደ ሰቱኝም ማለቱ ከፍተኛ ቃጠሎ ተነስቶ የሕንፃዎችን መደርመስና የእሳት ነበል ባል አያወጡም ማለቱ ነው ። በፊልም ውስጥ እንዳየው ማለት ነው ።


ይህ የሃያ ዓመት ጐረምሳ ቪቶሪዮ በመጽሐፉ ሌላ ገጽ ላይ ደግሞ«...በአይ ሮፕላን ዙርያውን ከበን እየዞረን በጥይት ስንቆላቸው አምስት ሺህ ያህል ኢትዮ ጵያውያን ባንድ ጊዜ ይረግፋሉ ። እነሱም የሚቃጠሉበት ጭስ ተመልካች ካለበት ሰማይ ድረስ ይደርሳል ።....አንድ ጊዜ በጋላ ነገዶች ላይ ያደረስኩት እልቂት ትዝ ይለኛል ። በጣም ብዙ ሆነው ተሰብስበዋል ። በመሀላቸው ጥቁር የለበሰ ሰው አየሁ ። ከዚያ ስብሰባ መሀልም አንድ ከባድ ፈንጂ ቦምብ ጣልኩ ። ያ የተሰበሰበ ሕዝብ እንደ ጽጌረዳ አበባ ከፍት ብሎ ሲረግፍ አየሁ ። እንዴት ደስ የሚል ነገር ነው ፤...» በማለት ጽፏል ።

ከአሸንጌው እልቅት የተረፈው ሠራዊት መጋቢት 27 ቀን ጉዞውን ወደ ኮረም ጀመረ ። ሠራዊቱ ኮረም ለመድረስ ጥቂት ሲቀረው የኮረም ከተማ በኢጣሊያኖች መያዟዋን ሰማ ። ከዚያም ተመልሰው በላስታ በኩል ወደ ደሴ ለመሄድ አሰቡ ። ቀን ቀን ተኝተው እየዋሉ ለሊት ለሊት ይጓዛሉ ። ይህ ሠራዊት እየገደለና እየሞተም ሚያዝያ 7 ቀን ንጉሡ ካሉበት ከላሊበላ ደረሰ ።


ከዚህ በኋላ ከንጉሡ ጋር ደሴ ገብተው ፣ ባለው ሰውና ደሴ በተቀመጠው ጥይት ለመዋጋትና የክተት አዋጅ ለማወጅ ከተወሰነ በኋላ እልጋ ወራሹ ሚያዝያ 6 ቀን ወደ አዲስ አበባ መሄዳቸውና የጠላት ጦርም እግር በእግር እየተከታተለ ደሴ ለመግባት መቸኮሉ ስለተሰማ እቅዱ ቀረ ።"...አንዲትም ጥይት ሳይተኩስ እልጋ ወራሹ ሸሸ ።..." በማለት አንጀሎ ይተቻል ።

የኢጣሊያ ሠራዊት ደሴን ለመያዝ ገሠገሠ። በቀን 50 ኪሎ ሜትር ያህል ይጓዝ ጀመር ። ከመቀሌ ጀምሮ ያለውን የመኪና መንገድ ሥራ ለማጣደፍ ሲባል መንገድ ሰራዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ወታደሩም እንዲሠራ ታዞ ስለነበር ሁሉም ጠመንጃቸውን እያነገቱ ከተራ ወታደር እስከ መኰንኖች ድረስ ያለው የኢጣሊያ ወታደር ሌትና ቀን ፣ ዝናብና ፀሀይ ሳይመርጥ ይሠራ ጀመር ። 150 ማይል ርዝመት ያለው የመ ኪና መንገድም በአራት ቀን ተሠርቶ አለቀ ።


የመንገዱ ሥራ በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ እየተጣደፈ ከሄደ በኋላ ባለሰንሰለት እግሮቹ 1725 ካሚዮኖች ወታደር ጭነው ባዶሊዮን አጅበው ሚያዝያ 12 ቀን 1928 ዓ. ም ደሴ ከተማ ገቡ ።



ለጦር እቅድ በአይሮፕላን የተነሳ የደሴ ከተማ ።




የደሴ ከተማ በቦምብ እንደተደበደበ ።



የክብር ዘበኛ መድፈኛ ክፍል ከባድ ተጋድሎውን ፈፅሟል ።



የደሴ አዲስ አበባ መንገድ ሲሰራ ።




ዶሴ ላይ አይሮፕላን ለመጣል የሚተኮሰው ተኩስ ።



አሸንጌ ።



በመርዝ ጋዝ የተቃጠለ የኢትዮጵያዊ እግር ።



በመርዝ ጋዝ የተቃጠለው የኢትዮጵያዊ እጅ ።

# ቦረና ነገሌ

በደቡብ ኢትዮጵያ ለሚሰለፈው የኢጣሊያ ጦር ጀኔራል ግራዚያኒ ጠቅላይ አዛዥ ሆኖ ተሹሟል ። እንደተሾመም ለጋዜጠኞች መግለጫ ሲሰጥ«...ዱቼ ኢትዮጵያን ይፈልጋል ። ኢትዮጵያን ከኢትዮጵያውያኖች ጋር ወይም ያለ ኢትዮጵያውያኖች እንደፈለገውና እንደወደደ ለሙሶሊኒ እንሰጠዋለን ።...» ብሎ ተናገረ ። ጀኔራል ናዚ ከዚህ መግለጫው በኋላ ሞቃዲሾ ገባ ።

ግራዚያኒ መቃዲሾ እንደገባ በመቃዲሾ አንድ ክፍለ ጦር የኢጣሊያ ወታደር ብቻ በማግኘቱ ለሙሶሊኒ በሚስጢር በላከው መልእክት«...በዚህ አቅጣጫ የሚያጋጥመን ውጊያ ቀላል ስላልሆነ የጦር ኃይል ይጨመርልኝ ። በተለይ ሐረር ከተማን ለመያዝ የተጠናከረ የጦር ኃይል ያስፈልገኛል ...» ብሎ አስታወቀ ። ዱቼ ሙሶሊኒም «እንደፈለግኸው ይሆንልሃል» የሚል መልስ ላከለት ። ከዚህ መልስ በኋላ ግራዚያኒ ኢትዮጵያ ወሰን ድረስ ያሉትን አዳዲስ መንገዶች በማሠራት ፣ የመቃዲሾን ወደብ አቀማመጥ በማስፋት ፣ በመቃዲሾ ከተማ ውስጥ የነበረውን የውሃ እጥረት በማሻሻልና ለወታደሩ ጉዞ የሚሆኑትን ሁሉ ሲያዘጋጅ ከረመ። ሞምባሳና ዳሬስላም ካሉ የእንግሊዝ ኩባንያዎችም በአሜሪካ የተሠሩ በመቶ የሚቆጠሩ መኪናዎችን ሲገዛ ሰነበተ ።

ግራዚያኒ ጦርነት በጀመረ ጊዜ 51.000ጠመንጃ ፣1585 መትረየስ ፣ 112 መድፍ ፣ 1800 መኪናዎች ፣ 7857 የጭነት እንስሳት ፣ ሰባ ታንኮችና 38 አይሮፕላኖች ነበሩ ። ይህም ቁጥር ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ የተጨመሩትን ሳይጨምር ነው ።

በኢትዮጵያውያን በኩል በራስ ደስታ ዳምጠው አዝማችነት 40.000 የሲዳሞና የባሌ ጦር ፣ በደጃች ነሲቡ ዛማኤል አዝማችነት 30.000 የኦጋዴንና የሐረርጌ ጦር ፣ በደጃዝማች አምደ ሚካኤል አዝማችነት 10.000 የአርሲ ጦር በየቦታው በደቡብ አቅጣጫ ተሰልፏል ።

በዱቼ ሙሶሊኒ ትእዛዝ የሰሜኑ ጦር የመረብን ወንዝ ሲያቋርጥ የግራዚያኒም ጦር በዚያው ዕለት ወሰን አቋርጦ ኦጋዴን ውስጥ ገባ ። በሶስት ሳምንት ጊዜ ውስጥም ቀላፎ ፣ ገርለጉቢ ፣ ቆራሄ እስከ ጥቅምት 28 ቀን ድረስ በኢጣሊያ ወታደሮች ተያዙ ።

በኢትዮጵያውያን በኩል የራስ ደስታ ጦር ከነገሌ እንስቶ ዶሎ ድረስ ያለውን ቦታ እንዲጠብቅ ስለታዘዘ በራስ ደስታ የሚመራው የባሌ ጦር ወደ ነገሌ ዞረ ። ይህም ጦር 400 ኪሎ ሜትር ያህል በእግሩ ተጉዞ ወሰን እንዲደርስ ተደረገ ። ጦሩ በሚጓዝበት ጊዜ ለአይሮፕላን አመቺ ሆኖ በመገኘቱ በአይሮፕላኖች ቦምብ እየተደበደበ ከሞት የተረፈው ከሶማሌና ከኢትዮጵያ ወሰን ዶርሶ ተሰለፈ ። የራስ ደስታ የጦር አማካሪ የነበረው ሌተና ፍሬር እንዲህ በሰልፍ ሆኖ መዋጋቱ የማያዋጣ ስለሆነ በሽምቅ ውጊያ ብንዋጋ ይሻላል ብሎ ነበር ። ተቀባይ ግን አላገኘም ።

የቀይ መስቀል አባል የነበረው ጁኖ ስለሲዳሞው ጦር በመጽሐፉ ሲያትት "......የሲዳሞን ጦር አዲስ አበባ ስገናኘው 15,000 ያህል ምርጥ ወታደር ነበረበት ። ከዚህም 15,000 ወታደር መሀል የተረፈው ከአራትና ከአምስት ሺህ አይበልጥም ።.....ጦሩን ያጠቃው የስንቁ ማለቅም ጭምር ነው ። በየቀኑ ከሶስት በሬ የበለጠ አይታረድም ። በዚህ ምክንያት የሥጋ ራሺናቸው በጣም ያነሰ ነው ።...

ሠራዊቱ ጫቄትም ይሰጠዋል ። ለአንድ ወታደር ለአንድ ሳምንት ቀለቡ የሚሰጠው ጫቄት በአንዲት ትንሽ ኩባያ ተሰፍሮ አንድ ኩባያ ብቻ ነው ። ለሠራዊቱ ቀለብና መሣሪያ የሚያመላልሱ ሁለት ካሚዮኖች አሉ ። እነኚህም ካሚዮኖች ብዙ ጊዜ ይሰበራሉ ። ተሠርተው ሲወጡም በመንገድ ላይ ሽፍታ ጭነታቸውን ያራግፈዋል ። ሠራዊቱ በረሃብ ደክሟል ። ከረሃቡ ሌላ ተቅማጥና የወባ በሽታ እንደ ዝንብ ያራግፋታል ።......"ብሏል ።

ይህን የኢትዮጵያን መንቀሳቀስ ያጠናው ማረሻል ባዶሊዮ በቴሌግራም ቁጥር 1897 ለግራዚያኒ መልእክት አስተላለፈ ። መልእክቱም "...የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ዋና ኃይል ወዳንተ መንዝ ጀምሯልና በእጅህ በሚገኘው በማንኛውም ዓይነት መሣሪያ በቦምብና በመርዝ ፣ ባለህ መሣሪያ ሁሉ መዋጋት አለብህ ። ከነዚህ በኋላ ምንም የሚያጠቃህ ያለ አይመስለኝም ። እርግጠኛ ነኝና እንደኔ ከሆነ ብታስብበት የሚከፋ አይመስለኝም ።..." የሚል ነበር ።

በሕዳር ወር ግራዚያኒ ዶሎ ገብቶ ጦሩን ሲያጠናክር ከረመ ። ዝግጅቱን ከጨረሰ በኋላ ሕዳር 28 ቀን 1928 ዓ.ም ወደፊት ለመግፋት ማሰቡን ጠቅላይ ጦር አዛዡን ባዶሊዮን ጠየቀ ። ባዶሊዮም "...እዚያው ሆነህ ተከላከል እንጂ አሁን ወደፊት አትግፋ ።..." አለው ። ግራዚያኒም "...ክሮማ ስመጣ የታዘዝኩት እንዳጠቃ እንጂ እንድከላከል አይደለም ። ለማጥቂያ እንዲያመቸኝም ብዬ አሁን ዶሎ ውስጥ 14,000 ወታደሮች ፣ 26 መድፍ ፣ 700 መኪና ፣ 3700 የጭነት አጋሰስ ፣ ብረት ለበስ መኪናዎችና ታንኮችን አሰልፌአለሁ ። ይህን ሁሉ ይዤ እንዴት ተከላካይ ሆኜ እቀመጣለሁ? ...." የሚል መልስ ለባዶሊዮ ላከ ። በግልባጭም ለሙሶሊኒ አስታወቀ ። ራሱ ግራዚያኒ በጻፈው መጽሐፍ ስለዚህ ጉዳይ ሲገልጽ "...ሙሶሊኒም እሳቤን ተቀብሎ ወደፊት ማጥቃት ይገባሃል የሚል መልስ ላከልኝና እኔም የማጥቃት ዝግጅቴን የበለጠ አዘጋጀሁ ። ከዱቼ ሙሶሊኒ ባገኘሁት የትዕዛዝ ሥልጣንም ኩራት ተሰማኝ ። ....."ብሏል ።

ጥር 4 ቀን 1928 ዓ.ም የመጀመሪያው ታላቅ ውጊያ ገናሌ ዶርያ ላይ ተካሄደ ። በዚያም ቀን በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ በምድር በታንክና በዘመናዊ መሣሪያ የሚደረገው ውጊያ እንሶ በአይሮፕላን 1700 ኪሎ ግራም የሚመዝን ቦምብና የመርዝ ጋዝ ተጣለበት ። ለዚያ ቦታ ውጊያ ግራዚያኒ ጦሩን በሶስት ቦታ ከፍሎት ነበር ። በጀኔራል ሞሬሊ ዲ ፖፖሎ የሚመራው ጦር በገናሌ ዶርያ ሸለቆ አልፎ እስከ ሳንዶር እንዲገፋ ፣ በመሀል በጀኔራል ቤርጉንዞሊ የሚመራው ጦር በፊልቱ አድርጐ በቦረናና በማኞ አልፎ እንዲጓዝ ፣ 3ኛው በጀኔራል አጉስቲኒ የሚመራው ጦር ደግሞ በዳዋ ፓርማ አድርጐ መልካ ሙሪ እንዲገባ ታዘዘ ። ግራዚያኒ ጦሩን እንዲህ አድርጐ ከከፋፈለ በኋላ የጦር አዛዦቹንና መኰንኖችን ሰብስቦ "....እናንተ በረሃ ገብታችሁ አውሬ የምታድኑ አዳኞች ናችሁ ። አዳኝ ከበረሃ ያደነውን አውሬ ለወገኑ እንደሚያካፍል ሁሉ ኢትዮጵያውያንን ለኢጣሊያውያን አደን አድኑዋቸው..." በማለት ንግግር አደረገ ።

በሶስቱም አቅጣጫ ወሰን አልፎ የገባው የኢጣሊያ ጦር የጉድጓድ ውሃና ወንዝ ካለበት ቦታ እየመሸገ ይቀመጥ ጀመር ። በዚህም አመሻሸጉ የኢትዮጵያን ሠራዊት ውሃ እንዳያገኝ አደረገው ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ከወንዝም ሆነ ከጉድጓድ ውሃ ለመቅዳት ወይም ለመጠጣት ሲጠጋ በየአካባቢው የመሸገው የኢጣሊያ ሠራዊት በመትረየስ ይገድለው ጀመር ። ይህም ግድያ ሰውን ብቻ በመምረጥ ሳይሆን እንስሳትና ግመሎች ሁሉ ውሃ ሲጠጡ ይገደሉ ጀመር ። ከላይ ከአየር ደግሞ አይሮፕላኖች በመመላለስ በመትረየስና በመርዝ ጭስ ይፈጁት ጀመር ።

በጀኔራል አውጊስቲኒ ጦር ውስጥ የነበረው ሳንድሮ ቮልታ ያየውን ሲገልጽ "...የቅናንት ማታው ትእይንት አሰቃቂ ነበር ። የውሃ ጉድጓዶች በእኛ እጅ ስለ

ነበሩ ኢትዮጵያውያኖቹ ውሃ ፍለጋ ሲርጡ ከፊታቸው ሞት ያለ አይመስላቸውም ። አበሾቹ ውሃ ለማግኘት ሲሮጡ መትረየስ ተኳሾቻችን ይጨርሷቸው ነበር ። ከመትረየሶቻችን ጥይት ተርፎ ውሃ ጠጥቶ የሚነሳው ወታደርም ከመሀላችን በመግባት ጉዳት ያደርስብናል ። በመጨረሻም በአይሮፕላን እየተረዳን አሸነፍናቸው ። አበሾቹ ለውሃ ፍለጋ የሚያደርጉትን ሩጫና እንደ አብድ በጥይት መሀል አቋርጠው ከመሀላችን ገብተው የሚያደርጉትን ተጋድሎ ማየቱ የተለዩ ፍጡራን ያስመስላቸዋል ። ከሠፈሩበት ቦታ ሁሉ የመርዝ ጋዝ ደጋግመን ባንጥል ኖሮ ድሉ የኢትዮጵያውያን ነበር ....” በማለት ጽፏል ።

በገናሌ ወንዝ አካባቢ ብቻ ስለተጣለው ቦምብ ቤርናባኪኒ የተባለ ጋዜጠኛ ሲገልጽ “...24 አይሮፕላኖች ሲደበድቡት ዋሉ ። ከሃያ አራቱ አይሮፕላኖች ስድስቱ መርዝ ብቻ የሚረጩ ነበሩ ። ዋዳ ካራ ላይ 1700 ኪሎ ግራም የሚመዝን የመርዝ ጭስና 7000 ቦምቦች ተጥለዋል ።....” ብሏል ።

ከእንዲህ ዓይነቱ እልቂት በኋላ የነጌሌ መንገድ ተከፈተ ። ከጥር 7 ቀን ጀምሮ የኢጣሊያ ሠራዊት በመንገዱ ላይ የሚያጋጥመውን ሁሉ እየገደለና እያቃጠለ ጥር 12 ቀን 1928 ዓ.ም. ነገሌ ቦረና ገባ ። ፓውል ጄንቲዞን ስለቦረና ነገሌ መያዝ ሲገልፅ “....ከተማዋን በታላቅ ደስታና ጭፈራ ገባንባት ። ከከተማዋ ስንገባም ምንም ዓይነት መሰናክል አላጋጠመንም ። እንዲትም ጥይት አልተተኮሰችብንም ።...” ይላል ። ይህ ሊሆን የቻለው አግረኛው የኢጣሊያ ጦር ከመንቀሳቀሱ በፊት አይሮፕላኖች እየቀደሙ በቦምብና በመርዝ ጭስ መንገዱን ይጠርጉለት ስለነበር ነው ። ለምሳሌ ቦረና ነገሌ ለመድረስ 40,000 ኪሎ ግራም የሚመዝን ቦምብ የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ጥለዋል ።

የኢጣሊያ ወታደር ቦረና ነገሌ እንደገባ እንደሰሜኑ ጦር ሁሉ በደቡብ ግንባርም ከኢጣሊያ ጋር የዘመቱ የኤርትራ ተወላጆች ወንድሞቻችንን አንወጋም በማለት ከኢጣሊያ እየከዱ ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር ተደባልቀዋል ። በደቡብ ጦር ግንባር ከዘመቱ የኤርትራ ተወላጆች መሀል ከኢጣሊያ ከድተው ከኢትዮጵያውያን ጋር የተደባለቁት የመጀመሪያው ሰው ሹምባሽ አንዶም ተስፋጽዮን ናቸው ። በጦር ሜዳ የወደቁትን የኢጣሊያኖችን ሬሣ ብቻ ጥቁር ተወላጆች እያነሱ እንዲቀብሩና የጥቁሩን ሬሳ እንደወደቀ እንዲተዉት ከኢጣሊያ አለቆቻቸው ጥቁር ወታደሮች ታዘዙ ። ሹምባሽ አንዶም ተስፋጽዮን ወደ ኢጣሊያዊው አለቃቸው ቀርበው “...ጥቁሮች ከነጮቹ ጋር አብረው ጐን ለጐን እንደተዋጉ ሁሉ በቀብር ጊዜ ለምን ልዩነት ይደረጋል ?” ብለው ጠየቁ ። ይህ ጥያቄ በኢጣሊያኖች ዘንድ እንደ ድፍረት ስለተቆጠረ ሹምባሽ አንዶም ተቀጡ ። ሹምባሽም ሌሊቱን አምልጠው ከኢትዮጵያውያን ጋር ተደባለቁ ። ከዚያ በኋላ ብዙ የኤርትራ ተወላጆች ከኢጣሊያ እየከዱ ወጡ ። ባንድ ቀን ሌሊትም 904 ሀማሴኖች ከድተው ከኢትዮጵያውያን ጋር ተደባለቁ ። ጁሴፔ ፑሊሲ እንደጻፈው “....ሹምባሽ አንዶም ተስፋጽዮን መክዳቱ ጐድቶናል ። ሹምባሽ አንዶም የተጠናከረ ኃይል ነበረው ። ....በሱ መክዳትም አንድ ሺ ያህል የኤርትራ ወታደሮች ከዱ ።...” ይላል ። አንዶም በአርበኝነት አራት ዓመት ያህል ሲዋጉ ቆይተው በ1931 ዓ.ም. አርማጮሆ ውስጥ በተደረገው ውጊያ ላይ ሞቱ ። ከሞቱም በኋላ ደጃዝማች ተብለዋል ።


የዶሎው ጦርነት ከተነሳ የአንዲት ኢትዮጵያዊት የማይታለፍ የጀግንነት ታሪክ አለ ። የእኚህን ኢትዮጵያዊት ስም አይጠቅስም እንጂ ዊልያም ማኪን በመጽሐፉ እንዲህ ይላል ። “....በዶሎ አካባቢ አበሾች በየተራራው ላይ መሽገው የኢጣሊያን መምጣት ይጠባበቃሉ ። የዚያ ቦታ ጦር መሪ የሆኑት የደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል ሚስት ከተራራ ላይ ሆና ስትመለከት የኢጣሊያ ወታደር ሲመጣ አየች ። የኢጣልያን ጦር ገፍቶ መምጣት እንዳየች የኢጣልያ ጦር መምጣት ላይ ነውና ይመታ ብላ ለባልዋ ነገረች ። ባልየው ግን ተጨነቁ ። የተጨነቁበትም ዋናው ምክ

ንያት ጥሩ የመከላከያ ቦታ ስለሌላቸው ከኢጣሊያ ወጥመድ እንዳይገቡ መጋጠሙን ፈሩ ።


“ከዚህ በኋላ ሚስቲቱ ከባልዋ ተለይታ ወደ ሌላ ሥፍራ ሄደች ። ከዚያም ልብስዋን ለዋውጣ እንደወንድ ለበሰች ። ፈቃደኛ የሆኑ 150 ሰዎች አዘጋጅታ ከጨረሰች በኋላ ከበቅሎዋ ላይ ወጥታ ወደፊት ገሠገሠች ። ሰዎችዋም የጦርነት ጩኸት እየጮኹ ወደሚመጣው የኢጣሊያ ጦር እየሮጡ ሄዱ ። የኢጣሊያ ወታደሮችም በቅሎ በምትጋልብ ሴት የሚመራ ጦር እንደመጣባቸው ባዩ ጊዜ ቦታ ቦታቸውን ይዘው ውጊያ ገጠሙ ።

“የአበሻው ጦር አዛዥ የሚስታቸውን ከጠላት ጋር መዋጋት እንደሰሙ ጦራቸውን ይዘው ለእርዳታ ሄዱ ። ደጃዝማች ከውጊያው ቦታ ሲደርሱ ውጊያው እልቆ ረዳት ከማያስፈልግበት ደረጃ ላይ ነበር ። ብዙ ኢጣሊያኖች ተገድለዋል ፣ ብዙዎች ቆስለዋል ። ያቺ አገርዋን የምትወድ ተዋጊ ሴት ከጠላትዋ ብዙ ጠመንጃና ጥይት ማርካ ተመለሰች ።...” በማለት ጽፏል ።


———o———




ከኢጣሊያ ሶማሌ የተንቀሳቀሰው የኢጣሊያ ጦር ።




ከኢጣሊያ ሶማሌ የተንቀሳቀሰው የኢጣሊያ ጦር ፡፡




ዶሎ ላይ የኢጣሊያ ምሽግ ።




የኢጣሊያ ጦር ዶሎ ሲገባ ።



ዶሎ የተከማቸው የኢጣሊያ ጦር ።




ዶሎ የተሰለፈው ጦር ።



መሬቲቱ ጋየች ።




የቦምቡ አወራረድ ።



ቦምቡ መሬቷን ሲያቃጥል ።



የነገሌው የውሃ መትረየስ ።



የንጉሡ ጉዞ ።



የንጉሡ ጉዞ ።

# የሐረር መያዝ

በቴሌግራም ቁጥር 1073/76 እ.ኤ.አ. ጥር 25 ቀን ጄኔራል ሩዶልፎ ግራዚያኒ ለዱቼ ሙሶሊኒ ሲያስተላልፍ «......ዱቼ ፣ የጠየቅኋቸውን መኪናዎች በቶሎ ይላኩልኝ ። እጅግ በጣም በአስቸኳይ የሚያስፈልገኝ ደግሞ ባለ 50 ፈረስ ጉልበት ያላቸው አንድ መቶ የሜካ መጥረጊያ መኪናዎችና 200 ባለሰንሰለት መኪናዎች በተጨማሪ ይላክልኝ ። እነኚህ ፈጠን ብለው በአስቸኳይ ከደረሱኝ ሐረር ከተማን ገፀ በረከት አቀርብሎታለሁ ።...» አለ ። እንደ ግራዚያኒ ጥያቄ እነኚህ መኪናዎች ፈጥነው አልደረሱም ።

የግራዚያኒ ችግር ይህ ብቻ አልነበረም ። ከኤርትራ ተወስደው በመቃዲሾ በኩል የዘመቱ ሀማሴኖች ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት እየከዱ አስቸግረውት ስለነበርም «...ከኤርትራ የተላኩልኝ የኤርትራ ወታደሮች እየከዱ ስላስቸገሩኝ በነሱ ምትክ የሊቢያ ወታደሮች ይምጡልኝ...» በማለት ለሙሶሊኒ ያሳለፈው ቴሌግራምም ፈጥኖ መልስ አላገኘም ነበር ። ይህ እስኪሟላለት ድረስም እወስን ድረስ መንገድ በማሠራት ቆየ ።

ጠቅላይ የአፍሪካው ጦር አዛዥ ማርሻል ባዶሊዮ «...ራስ ነሲቡን (ደጃዝማችናቸው) ለመግጠም ባሰብህ ጊዜ እንድታስታውቀኝ ይሁን ። ከቡርነትህ ወደፊት ለማጥቃት ከሄድህ ደግሞ ጠቅላይ ሠፈርህን የት እንዳደረግህ እንድታስታውቀኝ ። ምክንያቱም በራዲዮ ለመገናኘት እንዲያመቸን ነው ።...» የሚል ቴሌግራም ለግራዚያኒ ላከለት ። ግራዚያኒም በቴሌግራም ቁጥር 1757 M ሲመልስ «...ዝግጅቴ የተጓላ ስላልሆነ በአሁኑ ጊዜ ወደፊት ለመግፋት አሳብ የለኝም ። ባለኝ ባሁኑ ዝግጅቴ ወደፊት ገፍቼም በጠላት መያዝን አልሻም ።...» አለው ።

በዚህ ምልልስ ላይ እንዳሉ ሙሶሊኒ «...የጠየቅኸው የምድር ጦር እስኪሟላ በአየር እንድታጠቃ አዝዣለሁ ።...» በማለት ግራዚያኒን አዘዘ ። ግራዚያኒም ይህ ትእዛዝ ከደረሰው በኋላ ከመጋቢት 13 ቀን ጀምሮ መጋቢት 22 ቀን ድረስ ጂጂጋን ፣ ሐረርን ፣ ቡላሌን ፣ ቢርከትንና ደገሃቡርን በቦምብ ሲያስደበድብ ከረመ ። የእነኚህን ቦታዎች ደህና አድርጐ መደብደብና የምድር ጦሩም የተሟላለት መሆኑን ግራዚያኒ ለባዶሊዮ ካሳወቀ በኋላ በቴሌግራም ቁጥር 3714 «....እንግዲህ ብዙ ጦር ያከማቸው ነሲቡ የመመቸው ጊዜ መድረስ ያለመድረሱን በፍጥነት አስታውቀኝ ።...» ሲል ግራዚያኒ ፣ ባዶሊዮን ጠየቀ ። ባዶሊዮም በቴሌግራም ቁጥር 1897 ማይጨው ላይ ስላገኘው ድል ገልጾ «.... የንጉሡ ወታደር ወደ ደቡብ በመሸሽ ላይ ነው ። እሱንም ሁለት እግረኛ ክፍለ ጦርና አየር ኃይላችን ይከታተሉታል ። አሁን ሁሉንም አሽቀንጥሮ ለመጣል ጊዜው ደርሷል ። በዚህ ሁኔታ ክቡርነትዎም ድል ይቀዳጃሉ ።»ሲል ለግራዚያኒ መልስ ሰጠ ።

ይህን የሰሜኑን ድል የምሥራች የሰማው ግራዚያኒ ጦሩን «....አፕሪል 18 ቀን ለማንቀሳቀስ አስቤአለሁ ።...» ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ ባዶሊዮ በቴሌግራም ቁጥር 1947 አፕሪል 5 ቀን በሰጠው መልስ «...ግራዚያኒ ። የቆየኸው የጥንቱ የጦርነት ጓደኛዬ ። ሌላ ድል የምንቀዳጅበትን ጦርነት ቶሎ ብለህ ጀምር ።...» አለው ። እንደታሰበውና እንደታዘዘው ጦርነቱን ለመጀመር ጊዜው ደመናና ዝናብ ሆነ ። መኪናዎቹንም ጭቃ እየያዘ አላስሄድ አለ ። በግራዚያኒ ውስጥ ሆኖ ጦሩን የሚመራው ጄኔራል ናዚ «...በእንዲህ ዓይነቱ የአየር አፈና ባለበት ጊዜ ወደፊት መግፋቱ ጥሩ

አይሆንም ። ኢትዮጵያውያኖች እየተጠጉ ሲመጡ ያኔ መጋጠሙ ይሻላል ።...» በማለት ለግራዚያኒ አማክረና ምክሩ ተቀባይነት አገኘ ።

ናዚ እንዳለው ሁሉ የኢትዮጵያ ጦር ወደፊት እየተጓዘ ወደ ወሰን ተጠጋ ። በደጃዝማች አበበ ዳምጠውና በደጃዝማች መኩንን እንዳልካቸው የሚመራው ሠራዊትም ከወሰን 30 ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ጃኖጉቱ ላይ ሠፈረ ። ይህ አስር ሺ ያህል ሰዎች ያሉበት ጦር ከዚያ ቦታ መሽጐ ተቀመጠ ። በደጃች ነሲቡ ዘማኤል የሚመራው 28.000 ሰዎች ያሉበት ጦርም ወደ ወሰን ተጠግቶ ሠፈረ ።

ይህን የተጠጋውን የኢትዮጵያ ጦር ለመውጋት ግራዚያኒ ጦሩን አዘጋጀ ። በደገሃቡር ፣ በሳሳባኔና በቡላሌ በሶስት አቅጣጫ የዘመተውን የደጃች ነሲቡን ጦር ለማጠም 15.600 ነጭ ወታደሮች ያሉበት በጠቅላላው 38.000 ወታደር አዘጋጀ። አንደኛው ጦር በጀኔራል ናዚ የሚመራ ሲሆን ይህም ጃኖጉቱ የሠፈረውን የነደጃች አበበ ዳምጠውን ሠራዊት መትቶ በብርኩት ፣ በደከን ፣ በሰገግ አድርጐ ደገሃቡር እንዲገባ ታዘዘ ። በጄኔራል ፍሩስኪ የሚመራው የመሀሉ ጦር ደግሞ በሃማንሌና በሳሳበኔ አድርጐ ደገሃቡር እንዲገባ ተነገረው ። በጀኔራል አጉስቲኒ የሚመራው ጦር ደግሞ በኩራቲ ፣ በጉኑ ፣ በገዱ ፣ በቡላሌ አድርጐ እንዲጓዝ ተወሰነ ።

ይህ ዝግጅት ካለቀ በኋላ ሙሶሊኒ በቴሌግራም ቁጥር 4252 ለግራዚያኒ ሲያስተላልፉ «...ዛሬ አፕሪል 14 ቀን ቀዳሚው ጦራችን ደሴ እንዲገባ አዝዣለሁ።... ማንኛዋም ጊዜ በከንቱ መባከን የለባትም ወዳጄ ግራዚያኒ ። ወደ ሐረር የምታደርገውን ጉዞና የማጥቃት ወሬ እየተጠባበቅሁ ነኝ ።...» አሉ ። ግራዚያኒም ለዚህ ለደረሰው ቴሌግራም መልስ 150 ቃላት አዘጋጅቶ በቴሌግራም ቁጥር 4824/28 ከፊቱ የተደቀነው ጦር ኃይለኛ መሆኑን ገልጾ ካስረዳ በኋላ «....እአምሮዬን ክፍ የሚያደርጉልኝ አንድ እርስዎ ዱቼ ብቻ ነዎት ። ለአገሬ ለኢጣሊያና ለእርስዎ ለመሪዬ መቶ ጊዜ ብሞት የደስታ ሞት የምሞት መሆኔን ያውቁልኛል ።...ግን ትእዛዜን የማትቀበል ደደብ ነህ እያሉ ሰድበውኛል ።...አሁን እንዳሰብኩት ምን ዓይነት ሰው መሆኔን ለማሳየት ከመንገዴ ላይ የሚደቀነውን ሁሉ እየጠራረግሁ ለምን ድል አድርጌ አላስደስታቸውም ? ብያለሁ ። አደርገዋለሁ ።...» የሚል መልስ መላኩን ራሱ ግራዚያኒ በመጽሐፉ ገልጾታል ።

ሚያዝያ 7 ቀን በጀኔራል ናዚ የሚመራው ጦር ጃኖጉቶ ሊደርስ ሲል ጉራዋዲ የሠፈረው በደጃዝማች መኩንን እንዳልካቸው የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ተኩስ ከፈተበት ። በዚያም በረሃ ፣ ለበረሃ ያገለግላሉ ተብለው የተሰለፉት የሊቢያ ወታደሮች መከተው የኢትዮጵያን ጦር ተዋጉ ። በሁለቱም ወገን ድል ሳይገኝ ውጊያው እስከ ሚያዝያ 8 ቀን ድረስ ቆየ ። ኢትዮጵያውያኖቹ ጠንክረው በመዋጋታቸውና በማሲጋታቸው ሚያዝያ 9 ቀን በአይሮፕላን የቦምብ ድብደባውና የታንኮች ተኩስ ተበራከተ ። በተለይ እሳት የሚተኩሱ ታንኮች ደርሰው ኢትዮጵያውያን ያሉበትን ምሽግ በእሳት ተኩስ ያቃጥሉት ጀመር ። ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ሠራዊት ድል ለመሆን በቃ ።

የኢትዮጵያ ጦር ድል ሆኖ መንገዱ ከተከፈተ በኋላ የኢጣሊያ ጦር ሚያዝያ 10 ቀን ብርኩት ገብቶ ውሃውን ያዘ ። ውሃውን ከመያዙ በፊት ወደ ውሃው ሲያመራ ጊዜው ጨለማ ስለነበር ከጃኖጉቱ የተመለሰው የኢትዮጵያ ጦር ተኩስ ከፍቶ ከባድ ውጊያ ተደረገ ። ለሊቱን ሙሉ ሲታኮሱ አድረውና በነጋታውም ሲታኮሱ ውለው ኢጣሊያኖች እንደተለመደው በአይሮፕላንና በታንክ እየታገዙ ስላጠቁ የኢትዮጵያ ሠራዊት አፈግፍጐ ውሃው እኩለ ቀን ላይ ተያዘ ።

ሚያዝያ 15 ቀን በጀኔራል ናዚ የሚመራው ጦር ደጋመዶ ሲደርስ በጀኔራል ፍሩስኪ የሚመራው ጦር ደግሞ ሀማንሌይ ደረሰ ። የጀኔራል አውጉስቲኒ ጦር ደግሞ ከከባድ ውጊያ በኋላ ጉንጋዱ ደረሰ ። የጀኔራል ፍሩስኪም ጦር ቢሆን በሰ

ላም ሀማንሌይ አልደረሰም ። ሀማንሌይ ላይ ሰፍሮ የነበረው በፊታውራሪ መሊዮን የሚመራው ጦር ሁለት ቀን ሙሉ በጀግንነት ተዋግቶታል ። ጀኔራል ፍሩስኪ የኢትዮጵያን ጦር መበርታት አይቶ ለግራዚያን የጀኔራል አጉስቲኒ ጦር እንዲረዳው እንዲታዘዝለት ጠይቆ ነበር ። ግራዚያኒ ግን የጀኔራል አጉስቲኒን ጦር ማይሆን ገና ካልተነካው ከፓሪኒ ጦር ላከለት ። ይህም አዲስ የተላከው ጦር እሳት ብቻ በመተኮስ ስላጠቃ ፊታውራሪ መሊዮን ከሚመሩት ሠራዊት 600 ያህሉ ሞተ ። ከዚህ በኋላም ኢጣሊያኖች በቦምብም በጥይትም ያልቻሉትን የኢትዮጵያን ሠራዊት እሳት በሚተኩስ መሣሪያ በእሳት ኃይል ድል አደረጉት ።

ሐማንሌይ ላይ ስለተደረገው ጦርነት ሜጀር ፓውሎ ፔትሮኒ በማስታወሻ ደብተሩ ላይ አንዳንድ ነገሮችን ይዞ ነበር ። «....ከአበሾች ወታደሮች መሀል ሴቶችም አሉበት ። ግማሾቹ ሴቶች የወታደር ልብስ የለበሱ ሲሆኑ ግማሾቹ ደግሞ አለበሱም ። እነኚህ አደገኛ የአበሻ ተዋጊዎች አንድ ጊዜም ጠመንጃቸውን ከመተኮስ አላቆሙም ።...ከመማረክም መሞትን ስለሚመርጡ ብዙዎቹ በጦሩ ሜዳ ሲሞቱ የማረክናቸው በጣም ጥቂቶች ናቸው ። ከአበሾች ጋር ባደረግነው ጦርነት መሣሪያችን አኩልና የሚመጣጠንም አልነበረም ።...የሞተውን ሬሣ ቆጠርንና አንድ ሺ ሆነ ። የቆሰሉት ግን ካንድ ደርዘን አይበልጡም ። በጠቅላላ የማረክናቸው 36 ሰዎች ናቸው ። ከእነኚህም መሀል ሹማምንት ሲኖሩበት አንዲቱ ደግሞ ሴት ናት።..... በየትኛውም አገር ጦርነት ከሚሞተው ይልቅ የሚበዛው ቁስለኛው ነው ። በኢትዮጵያውያን ዘንድ ግን የተገላቢጦሽ ነው ።...በኢጣሊያውያን በኩል አስር መኰንኖች ሲሞቱ 11 መኰንኖች ቆሰሉ ። ከወታደሮችም አንድ ኢጣሊያዊ ወታደር ሲገደል ከነሱም እንደመኰንኖች 11 ቆሰሉ ። ከኤርትራና ከሱማሊያ ካሰለፍናቸው ወታደሮች ደግሞ 132 ሲገደሉ የቆሰሉት ግን 493 ናቸው ።...» ይላል ።


ኢጣሊያውያኖቹ እንደገለፁት በሶስቱ አቅጣጫ የዘመተው የኢጣሊያ ጦር አምስት ሺ ኢትዮጵያውያንን ሲገድል ከኢጣሊያ በኩል የሞተው ሁለት ሺ ወታደር ነው ብለዋል ። በእርጌ መሣሪያውና በራሱ ጥቂት ጥይት የተዋጋው የኢትዮጵያ ሠራዊት ከዚያ ዘመናዊ ትጥቅ ካለው ዘመናዊ ወታደር ውስጥ ሁለት ሺ መግደሉ የሚያስደንቅ ነው ።

ሚያዝያ 21 ቀን ሳሳቤህና ቡላሌ ተያዙ ። ሚያዝያ 22 ቀን ደግሞ ደጋሃቡር ተያዘ ። በደጋሃቡርም የኢጣሊያ ጦር ሠፈር አድርጐ ከረመ ። የከረመበትም ዋናው ምክንያት ዝናቡ እያየለ በመሄዱ ጭቃው መኪናዎችን አላስኬድ ስላለ ጠፍ እስኪል ድረስ ነው ። በዚህም ጊዜ በኦጋዴን የዘመተው የኢትዮጵያ ጦር ፣ አዛዥ የሌለው በየአለቃው የሚተዳደር ሠራዊት ነበር ። ዋናው የጦር አዝማች ነሲቡ ዛማኔል ሚያዝያ 25 ቀን ጂቡቲ ገብተው ከንጉሡ ጋር ተገናኙ ። በየአለቃው የተከፋፈለው የኢትዮጵያ ሠራዊትም ሰብሳቢ በማጣቱ ግማሹ ወደ እንግሊዝ ሶማሌ ገባ ። ግማሹም ወደኋላው ተመልሶ ጋራሙለታና ጨርጨር ተራራዎች ላይ እየወጣ ሸፈተ።


ዝናቡ ባራ እንዳለ ግራዚያኒ ጦሩን እየመራ ወደ ጂጂጋ ተጓዘ ። የኢጣሊያ ሠራዊት አንዳችም መሰናክል ሳያጋጥመው ጂጂጋ ገባ ። ግራዚያኒ ጂጂጋ ገብቶ የጂጂጋን ቤተ ክርስቲያን ሲጐበኝ ከቤተ ክርስቲያኑ ቀሳውስት አንዱ ጥይት ተኩሰው የግራዚያኒን እግር አቆሰሉት ። እኚያም ቄስ ወዲያውኑ በርብርቦሽ ተገደሉ ። በዚህ ቂም ይሆን ግራዝያኒ የኢትዮጵያ ገዢ ሆኖ በተሾመበት ጊዜ አቡነ ጴጥሮስን ፣ አቡነ ሚካኤልንና 425 የደብረ ሊባኖስ ቀሳውስትና ዲያቆናትን የገደለው ?

ግራዚያኒ በእስቶኢይ ሐረር ከተማን ከያዘ በኋላ ግንቦት 1 ቀን ድሬዳዋ ገባ ። ግራዚያኒ ድሬዳዋ በሚገባበት ጊዜ በወጣው ፕሮግራም መሠረት ባዶሊዮ በባቡር ድሬዳዋ ገብቶ ሁለቱ ድል አድራጊ መሪዎች በየተራ ለየድላቸው ሰላምታ ተለዋወጡ ።


በኦጋዴን ከዘመቱ ጦር መሪዎች መሀል ፊታውራሪ ጓንጉልን ፣ ታሪክ ፀሐፊው ፒር ኢካች አነጋግሮ ነበር ። ጠቅላላ ታሪካቸውን ለብቻ ጽፌዋለሁ ።



በኦጋዴን በረሃ የሰፈረው የኢጣሊያ ጦር ።




ኦጋዴን የገባው የኢጣሊያ ጦር በሰልፍ ቆሞ የግራዚያኒን ንግግር ሲያዳምጥ ።




ዋርዴር ላይ የተዘጋጀው የግራዚያኒ ዋና የጦር ሠፈር ።



በኦጋዴን በረሃ የኢጣሊያ ጥይት ሲጓዝ ።



ነጭ ወታደሮች የዋቤን ወንዝ ሲያቋርጡ ።



ዋቤ (ጁባ) ወንዝ ።